**DSpace Institution**

| | |
|---|---|
| **DSpace Repository** | **http://dspace.org** |
| Ethiopian Languages and Literature - Amharic | Thesis and Dissertations |


2015-11

# þÿè 3e õ- èp *Î}• èC u ÕÍ@u 3
# þÿKíód `0cp› -M p *Î} pp³*•u

þÿH•sì, • 4

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/14543

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት ዕውቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ፤ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት


በፈንታዬ ንጉሴ



ህዳር፣ 2015 ዓ.ም

ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

# የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ፤ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀግብር

የትምህርት ማስተር ዲግሪ በአማርኛ

በፈንታዬ ንጉሴ

የጥናቱ አማካሪ፤

ማስተዋል ውበቱ (ዶ/ር)

ህዳር፤2015 ዓ.ም

ባህርዳር፣ ኢትዮጵያ

## ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

### የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

### ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

"የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ፤ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ የትምህርት ማስተር ዲግሪ በአማርኛ (MEd in Amharic) ማሟያ በፈንታዬ ንጉሴ ይግዛው የቀረበ ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትን የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት፤**

አማካሪ፤

ስም፤ ዶ/ር ማስተዋል ውበቱ ፊርማ _________ ቀን_______________________ ዓ.ም

ፈታኞች፤

የውጭ ፈታኝ

ስም፤_______________________ፊርማ _____________ቀን__________________ ዓ.ም

የውስጥ ፈታኞች

ስም_____________________ፊርማ________ቀን__________________________ ዓ.ም

ስም _______________________ፊርማ ___________ ቀን___________________ ዓ.ም

# ማረጋገጫ

"የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ፤ በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ የትምህርት ማስተር ዲግሪ በአማርኛ (MEd in Amharic) ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን፣ የተገለገልኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መደረጋቸውንና ባህርዳር ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ስም፤ ፈንታዬ ንጉሴ ይግዛው**

ፊርማ፤ _________________ ቀን፤ ____________________

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይን ጥናታዊ ጽሁፍ ጀምሬ በሰላም እስካጠናቅቅ ስላምና ጤና ብርታቱን ጨምሮ ለሰጠኝ የእግዚአብሄር ስሙ የተመሰገነ ይሁን፡፡ ከርዕስ መረጣው ጀምሮ ስራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ የተሳሳተውን በማረም፣ ገንቢ ሀሳብ፣ አሰተያየትና ጥቆማ በመስጠት፣ የመረጃ መተንተኛ መንገዶችን በመፈተሽ ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ መምህሬና አማካሪዬ ዶ/ር ማስተዋል ውበቱ ምስጋና አቀርባለሁ፤ እድሜና ጤና አብዝቶ እንዲሰጥልኝ እመኛለሁ፡፡

ጥናቱን በተመለከተ ማንኛውንም ጉዳይ በስልክም ሆነ በመልእክት በጠየኳቸው ጊዜ ሁሉ በቅንነትና የሙያ ክብር በተሞላበት ሁኔታ አግዘውኛል፤ ስራዬን በጥልቅት በማየት እጅግ ጠቃሚ ከሆኑ አስተየየቶች ጋር በፍጥነት በመመለስ ጊዜየን በአግባቡ እንድጠቀምበት አግዘውኛል፡፡

በ2014 ዓ.ም በስማዳ ወረዳ በወገዳ ከተማ ዙሪያ በሚገኘው የወገዳ ሙሉ ሳይክል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ7ኛA እና በ7ኛC የመማሪያ ክፍሎች ትምህርታቸውን የተከታተሉ ተማሪዎች በጥናቱ ለመሳተፍ ፈቃደኛ በመሆን፤ እንዲሁም በፈተና መረጃዎችን በመስጠት ስለተባበሩኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በ2014 ዓ.ም በዚሁ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህርት የሆኑት ወይዘሮ ሀብታም መንገሻ ፍትነቱን በክፍል ውስጥ በመተግበር ስለረዱኝ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ የትምህርት ቤቱ ርዕሳነ መምህራንም ጥናቱን በትምህርት ቤቱ ለማካሄድ እንድችል ስለፈቀዱልኝ የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጥናቱን ወጪ በማገዝ ላደረገልኝ ድጋፍ ምስጋና ይገባዋል፡፡ ሃሳቤም ህልሜም እውን እንዲሆን ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ፣ የሞራልና የሙያ ድጋፍ በማድረግ ለረዳኝ ለውድ ባለቤቴ ለአቶ ፈንታ እንየው ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው፡፡ ስራዬን በኮምፒዩተር በመጻፍ ለረዳችኝ ለወይዘሮ ስመኝ ደርበው ፈጣሪ ረጅም እድሜና ጤና ይስጥልኝ እላለሁ፡፡

# አህፅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነበር፤ የጥናቱ ተሳታፊዎች በደቡብ ጎንደር ዞን በስማዳ ወረዳ በሚገኘው በወገዳ ሙሉ ሳይክል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በሰባተኛ ክፍል ተመዝግበው በመማር ላይ ከሚገኙት ስድስት የሰባተኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል በቀላል እጣ በተመረጡ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች የሚማሩ ተማሪዎች ነበሩ። ጥናቱ ፍትነት መሰል ቅድመትምህርት ፈተናና ድህረትምህርት ፈተና የቁጥጥር ቡድን (quasi-experimental pretest-posttest comparison group) ንድፍን የተከተለ ነበር። የፍትነቱ ቡድን ተሳታፊዎች (43 ተማሪዎች) በየሃሳብ ድር ብልሃት ቃላትን የማስተማር ብልሃት፣ የቁጥጥሩ ቡድን ተሳታፊዎች (45 ተማሪዎች) ደግሞ በክፍል ደረጃው የመምህር መምሪያና የተማሪ መጽሃፍ በተመለከቱት የማስተማሪያ ተግባራት መሰረት ቃላትን ለአስር ክፍለጊዚያት ተምረዋል። የቃላት እውቀትን የሚመለከቱ መረጃዎች በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት ፈተና ተሰብስበው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል። በቅድመትምህርት ወቅት የሁለቱም ቡድኖች የጥናቱ ተሳታፊዎች በቃላት ችሎታቸው ተመጣጣኝ እንደነበሩ የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ውጤቱ አሳይቷል። ከፍትነቱ በኋላ የፍትነቱ ቡድን ተሳታፊዎች ከቁጥጥሩ ቡድን ተሳታፊዎች በልጠው ጉልህ መሻሻል ማሳየታቸውን የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ውጤቱ ($t(86) = 2.98$, $P = .004$፣ $d = 0.63$) መሆኑን አመልክቷል። ከዚህ በመነሳትም የሃሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ጉልህ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አለው፤ ከማለት ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።ከዚህ ጥናት ውጤት መረዳት እንደተቻለው የፍትነቱ ቡድን ተማሪዎች በሃሳብ ድር ዘዴ ቃላትን መማራቸው የቃላት እወቅተ ፈተና ውጤት በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፤ በመሆኑም የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማጎልበት ብልሃቱን በተመለከተ በየድረጃው ለሚያስተምሩ ለቋንቋ መምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ስልጠና መስጠትና የቃላት ተግባራትንም ለዚህ ብልሃት በሚያመች መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

ከዚህ ጥናት ውጤት መረዳት እንደተቻለው የፍትነቱ ቡድን ተማሪዎች በሃሳብ ድር ዘዴ ቃላትን መማራቸው የቃላት እወቅተ ፈተና ውጤት በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፤

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

ማረጋገጫ ........ i
ምስጋና ........ ii
አህፅሮተ ጥናት ........ iii
ማውጫ ........ iv
የሰንጠረዥ ማዉጫ ........ vii
ምእራፍ አንድ፤ መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር ........ 4
1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄ ........ 7
1.4 የጥናቱ አላማ ........ 7
1.5 የጥናቱ ጠቃሚነት ........ 7
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 8
1.7 የጥናቱ ውሱንነት ........ 8
1.8 የቁልፍ ቃላት የጽንሰ ሀሳቦች ብያኔ ........ 9
ምእራፍ ሁለት፤ የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ........ 10
2.1. የቃላት ምንነት ........ 10
2.2. የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት ........ 11
2.3 በቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች ........ 13
2.3.1 ከመምህራንና ከተማሪዎች ተነሳሽነት አኳያ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች .. 13
2.3.2 የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት በተመለከተ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች ........ 14
2.4 ቃላትን ቀጥተኛ የማስተማር ብልሃቶች ........ 14
2.4.1 የትውስታ ብልሃቶች ........ 14
2.4.2 አእምሯዊ ብልሃቶች ........ 16
2.5 ኢ-ቀጥተኛ ቃላትን ማስተማር ብልሃቶች ........ 18

2.5.1 ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሀቶች ........ 19
2.5.2 ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች ........ 19
2.5.3 ማህበራዊ ብልሃቶች ........ 20
2.6 የሃሳብ ድር ብልሃት ........ 21
2.6.1 የሃሳብ ድር ብልሃት ምንነት ........ 21
2.6.2 የሃሳብ ድር ብልሃት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ........ 22
2.7 የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት ........ 24
2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 24
ምእራፍ ሶስት፤ የአጠናን ዘዴ ........ 32
3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 32
3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች ........ 33
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 34
3.4. የማስተማሪያ ምንባቦችና መልመጃዎች ዝግጅት ........ 36
3.5. የጥናቱ ሂደት ........ 37
3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 38
ምዕራፍ አራት፤ የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ ........ 40
4.1. የውጤት ትንተና ........ 40
4.2. የውጤት ማብራሪያ ........ 42
ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ........ 46
5.1. ማጠቃለያ ........ 46
5.2. መደምደሚያ ........ 47
5.3. አስተያየት ........ 47
ዋቢዎች ........ 50
አባሪዎች ........ 58
አባሪ ሀ ቅድመና ድህረ ትምህርት ቃላት ፈተና ........ 58
አባሪ ለ በሃሳብ ድር ቃላትን ማስተማር ዘዴ የተሰጠ ስልጠና ማንዋል ........ 62
አባሪ ሐ ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ለጥናቱ ተግበራ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ማንዋል ........ 68

አባሪ መ የፈተናውን አስተማማኝነት ለመፈተሽ በሙከራ ጥናቱን (pilot study) የተሰበሰበ መረጃ ........ 82
አባሪ ሠ የቅድመትምህርት ፈተናው መረጃ ........ 84
አባሪ ረ የድህረትምህርት ፈተናው መረጃ ........ 85
በአባሪ ሰ በቃላት እውቀት ፈተና የተገኙት መረጃዎች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ........ 87

# የሰንጠረዥ ማዉጫ

ሰንጠረዥ 3.1 የጥናቱ ንድፍ ........................................................................................ 32
ሰንጠረዥ 4.1 የቡድኖቹ የቅድመትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና ውጤት ፍተሻ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ........................................................................................ 40
ሰንጠረዥ 4.2 የፍትነት ቡድንና የቁጥጥር ቡድን የድህረትምህርት የቃላት እውቀት ውጤቶች ንጽጽርበነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ........................................................ 41

# ምእራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አላማ መግባባት በማስቻል ላይ የተመሰረተ ነው። የተግባቦት ስሜት ደግሞ በቃላት ህልውና ይረጋገጣል። በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ለሚካሄድ ተግባቦት ቃላት ወሳኝ ናቸው። Brown (2001) ቃላት የሌሎች የቋንቋ ክሂሎች መገንቢያ ብሎኬት እንደሆኑ ያስረዳሉ። Richards እና Renadya (2002) እንደሚገልፁት፣ ቃላት የቋንቋ ክሂሎች ቁልፍ ክፍል እንደሆኑና ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥ፣ መናገርና መፃፍ እንዳለባቸው የሚያስችሉ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር የሚያግዙ እንደሆኑ ይናገራሉ።

Nation (2001) የቃላት አጠቃቀምን ለቋንቋ ትምህርት በጣም አስፈላጊ አካል አድርገው ይመለከቱታል። ተማሪዎች በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቃላትን ይማራሉ። የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር ከሚያግዙት የቋንቋ ክፍሎች ውስጥ ቃላትን ማስተማር የቋንቋን ችሎታ ለማዳበር ከሚያስችሉት ዘዴዎች አንዱና ግንባር ቀደም እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ። ስለዚህ አንድ ሰው ብዙ የቃላት ትርጉም ባወቀ ቁጥር፣ ራሱን በጥሩ የቃላት እውቀት በማስታጠቅ፣ ሀሳቡን ሁሉን አቀፍና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ የመግለፅ ሁኔታ ይጨምራል (Nation እና Chung ፣2009)።

የቃላት እውቀት መኖር በተለይም በሳይንስና በማህበራዊ ጥናቶች በንባብ ሂደት አንብቦ ለመረዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን Hirch (2003) እንዲሁም Simmons እና ሌሎች (2010) ይገልጻሉ። ሆኖም ለተማሪዎች ይህን ለማሳካት ቀላል አይደለም። Ebbers እና Denton (2008)፤ እንዲሁም Rupely እና Nichois (2005) እንደገለፁት፣ የቃላት የእውቀት ደረጃ ከፍ የሚለው በግል የንባብ ተግባራትን በማሳተፍና በማበረታታት ይሆናል።

Nagy እና Anderson (1984) እንዲሁም Nagy፣ Herman እና Anderson (1985) እንደሚሉት የንባብ አቅማቸው ውስን የሆኑትና የመማር ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የግል አድርጎ የመጠቀም ሁኔታ አናሳ ነው። Bake፣ Simmons እና Kame'enui (1998) እና Chnningham እና Stanovich (1998) እንደገለፁት፣ ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የሚያስችሉ ብልሀቶችን በስራ ላይ በማዋል ካነበቡት ጉዳይ ቃላትን በመጠቀም ትርጉም ለማግኘት የሚያደርጉት ተሳትፎ አነስተኛ ነው።

የሃሳብ ድር ብልሃት የሃሳቦችን ስዕላዊ አቀራረብ እና ንድፍ መፍጠርን ያካትታል (Rabeka፣ 2014)፡፡ Budd (2003)፣ Fiktorius (2013)፣ Murley (2007) እና Hofland (2007) እንደሚሉት በሀሳብ ድር ቃላትን ማስተማር ተማሪዎች ቃላትን በተሻለ የሚማሩበትና የበለጠ ትርጉም ያለው ድግግሞሾችን የሚያከናውኑበት ነው፡፡

ስዕላዊ ንድፎችን በመጠቀም በሀሳብ ድር ቃላት ማስተማር የማስታወስ ችሎታን እና የተማሪዎችን መነሳሳት የሚያበረታታና ይበልጥ ግልፅ የሆነ የማስተማሪያ ድባብ ሊሰጥ ይችላል (Liu፣ Zahoና Bo፣ 2014)፡፡ የሃሳብ ድር እንደ ምስሎች፣ ቅርፆችና ቀለማት ያሉ ምስላዊ ፍንጮችን በመጠቀም እውቀትን ለማግኘት እና መረጃን ለማውጣት የሚረዳ ስዕላዊ ቴክኒክ ነው (Bud፣ 2004)፡፡ Miao (2007) እንደሚሉት ቃላትን በሃሳብ ድር ብልሃት ተጠቅሞ ማስተማር አዝናኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት፣ ጽንሰ ሃሳቦችንና ጭብጦችን በየጊዜው እንዲያጠኑ እና እንዲነቃቁ ለማነሳሳት ስለሚረዳ ነው፡፡

Aljarf (2011) አዕምሯዊ ፅንሰ ሀሳብን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል፤ Mind mapping (አዕምሯዊ ስዕል)፣ ስዕላዊ አደረጃጀት ሲሆን ዋና ተልእኮውም ከዋናው ሃሳብ በመነሳት የማፍለቅና ሌሎች ሀሳቦች የሚፈጠሩበት ነው፡፡ ሃሳቦችን ለማፍለቅ፣ ማሳታወሻዎችን ለመውሰድ፣ አስተሳሰብን ለማደራጀትና ፅንሰ ሀሳቦችን ለማዳበር የሚያገለግል ነው፡፡ የሃሳብ ድር ብልሃት የቃላት ትምህርት የሚረዳው ተማሪዎች ሃሳብን ለማስተዳደር፣ ትምህርትን ለመምራት እና ግንኙነቶችን ለመፍጠር የሚረዳ ገላጭ መሳሪያ ነው፡፡ ተማሪዎች በትምህርቱ ውስጥ የቀረቡትን ነገሮች በተሻለ ሁኔታ እንዲያደራጁ፣ ቅድሚያ እንዲሰጡና እንዲያዋህዱ ያስችላቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ የቃላት እውቀት የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ ዓላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በቃላት እውቀትና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክተው Tonjies (2000) እና Qian (2002) እንዳስረዱት፣ የቃላት ሀይል በአንብቦ መረዳት ስኬታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፤ ቃላት አንድን ጹሁፍ አንብቦ ለመረዳት ወይም ለማደናቀፍ ሊቆሙ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ በቃላት እውቀትና በአንብቦ መረዳት መካከል ጥብቅ ግንኙነት መኖሩን አመላካች ነው፡፡ በነባራዊው ሁኔታም ተማሪዎች በርካታ እንግዳ ቃላት ያሉበትን ጽሁፍ አንብበው ለመረዳት ሲሞክሩ በርካታ መሰናክሎች ሲገጥሟቸው ይታያል፡፡

እንደ አእምሯዊ የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ አራማጆች እይታ እዕምሯዊ እድገት ብልሀቶች አጠቃቀም እድገት መዳበር የተወሰነ ነው፡፡ ብልሃቶችን መጠቀምን ከበቂ ልምድ ጋር የተማሩ ተማሪዎች ብልሃቶችን በመጠቀም ልምዱ ከሌላቸው ተማሪዎች የበለጠ ይማራሉ (Omalley እና Chamot፣ 1990)፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች የቃላት ትምህርት የተለያዩ ብልሃቶች አጠቃቃም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል (Nikos፣ 2007 እና Schmitt፣ 1998)፡፡

ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከመነሳቱ ጋር የቃላት እውቀት በቋንቋ ትምህርት ወሳኝ ሚና እንዳለው የመስኩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ የማስተማር ዘዴ ከቅርፅ ይልቅ ትርጉም ላለው መስተጋብራዊ ተግባር አፅንኦት ስለሚሰጥ ስኬታማ ተግባቦት ለማከናወን የቃላት እውቀት መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑ እንዲታወቅ አድርጓል (Allen፣1983፤Carter እና McCarty፣ 1998 Schmitt፣ 2000)፡፡

በተግባቦታዊ አቀራረብ መሰረት የተማሪዎች የቃላት እውቀት ማደግ የሚችለው ተማሪዎች ራሳቸው የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ተዋናይ በመሆን በንቃት ሲሳተፉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በቋንቋ ትምህርት በራስ መር መማርና ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረጉ ተማሪዎች ቃላትን በራሳቸው አንዲማሩ ለቃላት አጠቃቀም አፅንኦት ስለሚሰጥ በቃላት ትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ አድርጓል (Tudor፣1996፤ Gains እና Redman፣ Oxford፣ 1990)፡፡

ቃላትን የማስተማር ብልሀት አስፈላጊነትም የተለያዩ ንደፈ ሀሳዊ መነሻዎች አሉት፡፡ እንደ Omalley እና Chamot (1990) ገለፃ አዕምሯዊ ንቃት ያለው ተማሪ የበለጠ ይማራል የሚለው የአዕምሯዊ የማስተማር ንድፈ ሀሳብ የዚህ ሀሳብ ደጋፊ ነው፡፡ ተማሪዎች ልዩ ልዩ የመማር ተግባራትን በንቃት ተቀብለው በማደራጀት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ማዛመድ የሚችሉ ልዩ ልዩ የማስተማር ብልሀቶችን መርጠው ሲተገብሩ ነው ከሚል መነሻ የመነጨ ነው፡፡ ተማሪዎች እንዴት መማር እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡ ብልሃቶችን ማወቃቸውና መተግበራቸው ዋነኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚረዳቸው Wlliams እና Burdn (1997) ያስረዳሉ፡፡

Brown (1994)ም መስተጋብራዊ፣ ውስጣዊ ተነሳሽነትና ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብ አስፈላጊነቱ በሚወሳበት ዘመን ተማሪዎች መማርን የሚረዱ ብልሀቶች እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ እንደ Harmer (1991)፣ Rechards እና Renanda (2002)

አገላለፅ ቀደም ሲል የተለያዩ የቋንቋ መርሀግብሮች ሲዘረጉ የቃላት ትምህርት የታላሚው ቋንቋ መዋቀር ለማስተማር እንደመሸጋገሪያ ይታሰብ ነበር፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የቃላት ትምህርት ትኩረት እያገኘ እሰቤውም እየሰፋ መጥቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የሃሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳድግ ያለውን ፋይዳ መመርመር አስፈልጓል፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

የቃላት ትምህርት ለተግባቦታዊ ስኬት መሰረት በመሆኑ በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ወይም ደረጃዎች በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ ሰዎች ቋንቋን እንዲማሩ ከሚያስገድዷቸው ምክንያቶች ተግባቦታዊ ብቃትን ማዳበር አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ የቃላት እውቀት ተማሪዎች አዲስ ፅንሰ ሀሳብን በፍጥነት እንዲረዱ ያግዛቸዋል፤ በዕለት ተዕለት የተግባቦት ክዋኒያቸው የተሻሉ፣ ማህበራዊ ግንኙነታቸውም የተሳካ እንዲሆን ይረዳቸዋል (Nation፣ 2001)፡፡

ከ1980ዎቹ አጋማሽ ወዲህ በቃላት ትምህርት አኳያ በርካታ ጥናቶች ተከናውነዋል (Nation፣ 2001)፡፡ ይሁን እጅ አብዛኛዎቹ ጥናቶች ተደራሽ በሆኑት ጥናታዊ መፅሄት ላይ የታተሙ ባለመሆናችው ብዙ የቋንቋ መምህራን አያውቋቸውም፡፡ በመሆኑም በመምህራን የቃላት ትምህርት አመለካከትና አተገባበር ላይ ያመጡት ለውጥ ዝቅተኛ ነው፡፡ Schmitt (1997) እና Oxford (2003) እንደሚጠቁሙት ከ1980ዎቹ በኂላ የተከናወኑ የምርምር ውጤቶች ተማሪዎች ክፍል ውስጥም ሆነ ክፍል ውጭ አዳዲስ ቃላትን በተለያዩ የቃላት መማሪያ ብልሃቶች አማካይነት በራሳቸው መንገድ በቀላሉ እንዲማሩ የሚያግዙ ናቸው፡፡

Liu፣ Zhao እና Bo (2014) ያካሄዱት ጥናት ውጤት እንዳመለከተው ቃላትን በመማርና በማስተማር የሀሳብድር ብልሃት ለቃላት እውቀት ጠቃሚና ውጤታማ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ Macaro (2001) እንዳስረዱት ቃላት ሀሰብን ለመቀበልም ሆነ ለማስተላለፍ መስረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እንዲሁም Read (2000) የቃላት ትምህርት ወሳኝና ቀዳሚ ጉዳይ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጅ ለቃላት ትምህርት ተገቢ የሆነ ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቷል፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪዎች የተግባቦት ችሎታ ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር ጉዳይ ነው፡፡

የቃላት ችሎታ ብዙ ቃላትን ከማወቅ ባለፈ የተለያዩ የቃላት ማስተማር ብልሃቶችን የመጠቀም ብቃትንም ያካትታል (Read፣2000)፡፡ ከዚህ አኳያ በቃላት ትምህርት መስክ ቃላትን ለማስተማርና ለመማር የሚያገለግሉ በርካታ አቀራረቦች፣ ቴክኒኮችና ብልሃቶች

ተነድፈዋል (Hatch እና Brown፣ 1995፤ Nation፣ 2001)፡፡ የቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በርካታ የቃላት ክምችት እንዲኖራቸው መምህራን ተማሪዎቹን ለመርዳት የትኛው ብልሃት የቃላት እወቀታቸውን ለማሻሻል አማራጭ እንደሆነ ሊያውቁ ይገባል (Oxford፣ 2003)፡፡

ከአዳዲስ የቃላት እውቀት ለመዳ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች ዋቢ አድርገው Wong (2005) እና Nation (2001) እንዳስረዱት ተማሪዎች የቋንቋ ቃላት እውቀታቸው ውስን ከሆነ በቋንቋው በአግባቡ ለመግባባት ይቸገራሉ፡፡ በቂ የቃላት እውቀት ያላቸው ተማሪዎች እውቀቱ ከሌላቸው ተማሪዎች በበለጠ አንድን ጽንሰ ሃሳብ በፍጥነት መረዳት እንደሚችሉም የጥናት ውጤቶች ያመለክታሉ፡፡

ከምርምር ውጤቶች መረዳት እንደሚቻለው የቃላት ማስተማር ብልሀቶችን በስፋት ማስተማር ተማሪዎች በተምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛል፡፡ Nunan (1991) እንደሚያብራሩት ቃላትን ማስተማር ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ቃላትን ለመማር የሚያስችሉ ሁኔዎችን ማመቻቸትም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የሚያስችሉ ዘዴዎችንና ብልሃቶችን የሚተዋወቁበትንና የሚለማመዱበትን እድል ካገኙ የቃላት እውቀታቸው ሊዳብር ይችላል፡፡ የሃሳበ ድር ብልሃት ቃላትን በማስተማር አኳያ ያለውን ፋይዳ አስመልክቶ በውጭ ሀገር የተካሄዱ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡

Anders (1984)፣ Bos እና Allen (1989)፣ Bos እና Anders (1992)፣ Fore፣ Bos እና Owrie (2007) ለአብነት ያህል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ጥናቶቹ ቃላትን በማስተማር ሂደት የሀሳብ ድር ብልሀት ፋይዳ ምን ያህል እንደሆነ ፈትሸዋል፡፡ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናቶቹ ግኝትም ብልሃቶችን የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ ቃላትን ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በድህረትምህርት የቃላት ፈተና የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ጠቁመዋል፡፡ ሆኖም ጥናቶቹ የሀሳብ ድር ብልሃት የቃላት እውቀትን እንደሚያሳድግ ከማሳየት ባሻገር የጥንካሬ ደረጃውን (Efect Cize) አላመለከቱም፡፡

እንዲሁም የቃላት እውቀትን ለማሳደግ ያለውን ሚና የፈተሹ የሃገር ውስጥ የሁለተኛ ዲግሪ መሚያ ጥናቶችም ተካሂደዋል፡፡ ብሩክታይት (2001)፣ እሸቱ (1997) እና ደረበ (1999) የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ከዘመናዊ የቃላት ትምህርት አቀረቀረብ

ያለውን ተገቢነት ለመፈተሽ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚተገበረው የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት ውጤታማነታቸው በተፈተሹ የቃላት ማስተማሪያ ብልሃቶች ሊካሄድ እንደሚገባው እነዚህ ጥናቶች ይመክራሉ፡፡ ይህም፣ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ የቃላት ማስተማሪያ ብልሃቶችን ውጤታማነት በጥናት እየፈተሹ በስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

ንጋቱ (2000) እና በላይነሽ (2002) አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ለመፈተሽ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው ግኝትም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች (በላይነሽ፣ 2002) እና አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች (ንጋቱ፣ 2000) ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በመጠቀም ላይ የተመሰረተ አለመሆኑንና የቃላት ችሎታቸውም ዝቅተኛ መሆኑን አሳይተዋል፡፡

የጥናታቸውን ውጤት መነሻ በማድረግም በክፍል ውስጥ የሚተገበረው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዘመናዊ የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ ስልቶችን የተከተለ እንዲሆንና የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ማዳበር እንዲችል መምህራን ተማሪዎቻቸው ከተለያዩ ብልሃቶች ጋር እንዲተዋወቁ በማገዝ በራሳቸው ጥረት ቃላትን እንዲማሩ መርዳት እንደሚገባ የመፍትሄ ሐሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ይህም በቃላት ትምህርት ዙሪያ ያላቸውን ችግር ከማሳየቱ በተጨማሪ የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ችሎታ መዳበር የቃላት ችሎታቸው እንዲሻሻል ንድፈሃሳባዊም ሆነ ተግባርዊ ስልጠና መስጥት እንደሚያስፈልግና ለቃላት ችሎታ መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፤ቢባል ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል፡፡

አጥኝዋም አማርኛን በከፍተኛ ሁለተኛ ድረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በማስተማር ልምዷ ያስተዋለችው ተማሪዎች የቃላት እውቀት ላይ ችግር እንደሚገጥማቸው ነው፡፡ ምክኒያቱም የማስተማሪያ ብልሃትን ያልተከተለና ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቃላት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ የተለያዩ የቃላት ማስተማር ብልሃቶችን ከማስተዋወቅ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አንብቡና መልመጃዎችን ስሩ፣ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቻቸውን ፈልጉ ወዘተ. በሚል የተለመደ

አካሄድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለተማሪዎች በማያሳትፍ ነው፤እውቀትን ከመገንባት ይልቅ እውቀትን በማስተላለፍ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደተጠቀሰው አጥኛዋ ባደረገችው በቃላት ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶች ቢኖሩም በአማርኛ ቋንቋ የሀሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እወቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ በሚል ጥናት የተጠና አላገኘችም፡፡ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ የፈተሸ ሙከራዊ ጥናት በወገዳ ሙሉ ሳይክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለማግኘቷ ለጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ሁኗል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄ

የዚህ ጥናት ጥያቄ "የሃሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እወቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?" የሚል ነው፡፡

## 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሀሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፈይዳ መመርመር ነው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቃሚነት

ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የሚታዩባቸውን ተላውጦዎች መለየት ለመማር ማስተማሩ ሂደት የላቀ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ከዘህ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ስነትምህርታዊና ምርምራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡

1. ስነትምህርታዊ ፋይዳው ለተማሪዎች ቃላትን የማስተማር ብልሃቶችን በቃላት ትምህርት ሂደታቸው በመጠቀም የቃላት እውቀታቸውን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ የሚያሳይ ብልሃት እንዲያገኙ ያግዛል፡፡
2. ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት/ መርሀትምህርት ባለሙያዎች የማስተማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች በትምህርት መሳሪያዎቹ መካተት የሚገባቸውን የሀሳብ ድር የተሰኘውን የቃላት ማስተማሪያ ብልሃት ውጤታማነት በሚፈለገው ደረጃ አሻሽለው እንዲያቀርቡት መረጃ ይሰጣል፡፡

3. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት የማስተማር ብልሃቶች ለቃላት እውቀት መጎልበት ያላቸውን ፋይዳ በመገንዘብ ተማሪዎቻቸው በቃላት ትምህርት ሂደት ብልሃቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ግንዛቤ ሊያስገኝ ይችላል፡፡

ምርምራዊ ጠቀሜታው ደግሞ ሌሎች ተመራማሪዎች በቀሪ የቃላት ማስተማሪያ ብልሃቶች የቃላት ትምህርት ላይ ለሚያደርጓቸው ጥናቶች መነሻ ይሆናል፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ያተኮረው በደቡብ ጎንደር ዞን በስማዳ ወረዳ በወገዳ ከተማ ከሚገኙ አምስት ሙሉ ሳይክል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በወገዳ ሙሉ ሳይክል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነው፡፡ ከክፍል ደረጃና ከተማሪዎች አንፃርም ሁለት የሰባተኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የፈተሸውም የሃሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎች የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውሱንነት

የዚህ ጥናት ቀዳሚ ውሱንነት መረጃ የተሰበሰበበት የቃላት ፈተና በአጥኝዋ የተዘጋጀ መሆኑ ነው፤ መደበኛ (standardized) ባለመኖሩ ፈተናው በአጥኝዋ ተዘጋጅቷል፡፡ ምንም እንኳን አስተማማኝነቱንና ተገቢነቱን በተለያዩ መንገዶች ለመፈተሽ ቢሞከርም ብቃቱን ሙሉ በሙሉ ለማስጠበቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ ውጤት ላይ የተወሰነ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ሁለተኛው የጥናቱ ውሱንነት የፍትነት ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ በአንድ ትምህርት ቤት መገኘታቸው ነው፤ ምናልባትም የፍትነት ቡድኑ ተሳታፊዎች የፍትነቱን ሁኔታ አስመልክቶ ለቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች መረጃ ሊያደርሱ ይችላሉ፤ ይህም በፍትነቱ ውጤት ላይ የተወሰነ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡

ሶስተኛ፣ የቃላት እውቀት ትምህርቶች በተቀራረበ ጊዜ አለመተግበራቸው ( በሁለት ሳምንት አንድ ክፍለዚዜ ብቻ መተግበራቸው ነው)፡፡ በመደበኛው ክፍለጊዜ የሚሰጠው የቃላት ትምህርት በመምህር መምሪያውና በተማሪው መጽሀፍ ላይ በሳምንትና በክፍለጊዜ ተወስኖ በመስፈሩ የቃላት ትምህርቶቹን ክፍለጊዜያቸውን (የሳምንቱን ሁለት መደበኛና አንድ ማካካሻ

ክፍለጊዜ) ለሁሉም ይዘቶች ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ በመሆኑ የቃላትን በሃሳብ ድር ብልሃቱን ማስተማር  ክፍለጊዜ እየጠበቁ መተግበር ግድ ሆኗል፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላት የጽንሰ ሀሳቦች ብያኔ

የሃሳብ ድር ብልሃት፤ የተማሪዎችን የቃላት እውቀታቸውን ለማሻሻል የሚጠቀሙበት ብልሃት ነው፡፡ የሃሳብ ድር ብልሃት ተማሪዎች የቃላትን ፍች ማለትም የቃላትን ተመሳሳይ ፍች፣ አውዳዊ ፍች፣ ተቃራኒ ፍች ወዘተ. ቃላትን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚየሳይ ብልሃት ነው፡፡

የቃላት እውቀት፤ ሰዎች ቋንቋ እንዲማሩ ከሚየስገድዷቸው ምክኒየቶች ዋነኛው ተግባቦታዊ ብቃትን ማዳበር እስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና አለው፡፡

ምክንያቱም ስለአንድ ነገር በአግባቡ ማዳመጥ፣ መናገር፣ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ከቃላት እውቀት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው፡፡ በቂ የቃላት እውቀት ያላቸው ተማሪዎች እንድን ጽንሰ ሀሳብ በፍጥነት መረዳት ይችላሉ፤ የተለካውም በተመራማሪዋ በተዘጋጀ ፈተና ነው፡፡

# ምእራፍ ሁለት፤ የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1. የቃላት ምንነት

የቃላት እውቀት በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በተግባቦት ቋንቋን የማስተማር ሂደት በስፋት መሰጠት የተጀመረው ከ1990ዎቹ ጀምሮ ነው፡፡ ይህ ቋንቋን በተግባቦት የማስተማር ሂደት ከሌሎቹ የማስተማር ሂደቶች የተሻለና በአሁኑ ወቀት በሰፊው በአለም ላይ ተቀባይነት ያገኘ ነው፡፡

በተግባቦት ቋንቋን የማስተማር ሂደት በጥንታዊ ቋንቋ ማስተማር ሂደት ስር ተደብቆ የቆየ ቢሆንም ጠቃሚነቱ ታይቶ ስራ ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ የቋንቋ ማስተማሪያ ሂደት ሁሉም የተስማሙበትና እንደ አንድ ስርዓተ ትምህርት ተወሰወዶ በተለየ መንገድ ስራ ላይ እየተተገበረ እንደሚገኝ የመስኩ ባለሙያዎች ያስረዳሉ (Richards፣ 2002)፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስኬታማ ተግባቦት ለማድረግ የቃላት እውቀት ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የቃላት እውቀት የሚባሉት የሆሂያት፣ የንበት፣ የቃላት ፍች፣የቃላት አገባባዊ፣ የሰዋሰው ህግጋትና የአራቱ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ መጻፍና ማንበብን) ሁሉ የሚያካትት ነው (Nation፣ 2001)፡፡ ቀደም ሲል የነበሩበት አመለካከቶች በወቅቱ ለቃላት ትምህርትና ጥናት ትኩረት እንዲሰጥ ባያደርጉም ከበርካታ አስርት ዓመታት በኋላ የቃላት ትምህርትና ጥናት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠበት ነው፡፡

በ1980ዎች እ.አ.አ በመዝገበ ቃላት ላይ ጥናት ከተካሄደ በኋላ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ የቃላት እድገት እየጨመረ መጥቷል (Zimmerman፣ 1997):: በ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ቃላትን የማስተማር ትኩረት የተሰጠው በአብዛኛው ለተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በቋንቋ ውስጥ ከመጡበት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም ዘዴው ከቅርፅ ይልቅ ትርጉም ላለው መስተጋብራዊ ተግባር አፅዕኖት ስለሚሰጥ ነው፡፡ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ በውሰጡ ብዙ ጥገኛ ምዕላዶችን ሊይዙ የሚችሉና ከቃል ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ሊመደብ የሚችል ቃል ይባላል (ባየ፣ 1987)፡፡ ቃላት ትርጉም ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ አሀዶች ናቸው፡፡ እነዚህ አሀዶች ደግሞ ወደ አነሰተኛ ትርጉም አዘል አሀድ ሊከፈሉ አይችሉም፡፡ ይከፈሉ ቢባል እንኳን ትርጉም አልባ ድምፆች ይሆናሉ፡፡ ስለሆነም ምዕላዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ራሳቸውን ችለው በመቆምና ከዚያ ወደ አነሰተኛ አሀድ ሊከፈሉ

ባለመቻላቸው ምዕላድ ሲሆን፤ ራሱን ችሎ በመቆሙ ብቻ ደግሞ ቃል ነው። ከዚህ በመነሳት ቃል በውስጡ ቢያንስ አንድ ብቻውን ሊቆም የሚችል ነፃ ምዕላድ ይኖረዋል (ባየ 1987፤ McCarthy፣ 2002)::

አንድ ቃል ብዙ አይነት ፍቺና የፍቺ ማዕረግ ሊኖረው ይችላል። የአንድ ቃል ፍቺ በብዙ ስልት ሊጠብ፣ ሊሰፋ፣ ሊሻሻልና ሊወሰን ይችላል። አንድ ቃል መደበኛ ፍቺ ይኖረዋል። ለማጥበብም ሆነ ለመስፋት፣ ለመሻሻልም ሆነ ለመወሰኑ መሠረቱ የቃሉ መደበኛ ፍቺ ነው (ብርሃኑ፣1997)። ስለዚህ ቃላት የንግግር መሳሪያዎች ሆነው ስሜቶቻችንን፣ ፍላጎታችንን፣ አመለካከቶቻችንን፣ ደስታዎቻችን የተለያዩ የስራ ክንውኖቻችንን ለመግለፅ የምንችልባቸው የቋንቋ ንዑሳን ክሂሎች ናቸው። የማንኛውም ቋንቋ ህልውና ያለ ቃላት ማሳየት ከቶ አይቻልም። ከስረዓታዊ ባህሪያቸው አንፃር ስንመለከታቸው ቃላት በንግግር ድምፆች ቅድመ ተከተላዊ ቅንጅት የተመሰረቱ ወይም የተዋቀሩ፣ የተለያዩ ሙያዎችንና ፅንሰ ሀሳቦች መገለጫነት ውክልና የቆሙ የአንድ ቋንቋ አካል ናቸው።

## 2.2. የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት

ቃላት በክፍል ውስጥ ይቀርብ የነበረው የቋንቋውን መዋቅር ለማስተማር ሲባል ነበር። ለዚህም ምክንያት Allen (1983) እንደሚያስረዱት፣ የቋንቋ ምሁራን ከቃላት ይልቅ ለሰዋሰው ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው፤ ሲሆን ይህንንም ያደርጉ የነበረው በቂ የሰዋሰዋው ችሎታ ከመያዛቸው በፊት በርካታ ቃላት ቢያውቁም በእፍተነገር ምስረታ ላይ ስህተት ይፈጽማሉ የሚል ስጋት በመያዛቸው ነው። Allen አያይዘውም፤ የቃላት ትምህርት ተኩረት የቆየ ቢሆንም በዚህ ወቅት ቃላትን ማስተማር ምንም የማያሻማ መሆኑ ታምኖበት በአግባቡ መቅረብ ላይ ያለ የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ መሆኑን ገልፀው፤ በተግባቦት ሂደት ውስጥ መሰናክል የሚፈጥረው በቂ የቃላት እውቀት ባለመኖሩ እንደሆነም ያምናሉ። ስለዚህም ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋሰው እስኪያውቁ ድረስ የቃላት ትምህርት የማይዘነጋ መሆን እንዳለበት አሰረድተዋል።

Little (1994) እንደሚያስረዱት፣ በቋንቋ አጠቃቀም ወቅት ዋናው ችግር ቃላትን ረቂቅ በሆነ መዋቅር ማዛመዱ ሳይሆን ቃላቱ አንዳቸው ከአንዳቸው ጋር በማዛመድ ማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ግልፅ እንዳደረጉ ለይቶ ማወቁ ላይ በማለት ከሰዋሰው ይልቅ ቃላትን

ቀድሞ ማስተማር እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፡፡ በቃላት ምንነት ዙሪያ ብሎምፊልድ የድርሻውን ብሏል፡፡ ይኸውም ቃላትን እንደ ዝቅተኛና ነፃ ቅርፅ አድርጎ ያቅርባል፡፡ በቃላት ብያኔ ላይ የዳኛቸው ወርቁን አተያይ ብንመለከት ቃል በአንደበት ወይም በፊደል ምትክነት የሚገልፅ የሀሳብ (ስሜት) ወካይ ነው (ዳኛቸው፣1977)፡፡

በነዚህና በሌሎችም ስነልሳን ምሁራን ግንዛቤ ስለቃል ሰፋ ያለ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ፡፡ የስለምንነቱ ከመረዳት ባሻገር ደግሞ ቃላት በተግባቦት ሂደት ሚና አለው፡፡ ይህ ሚናው ደግሞ ቋንቋውን ጥቅም ላይ ለማዋል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ተማሪዎች በቋንቋ የሚፈጥሩት ተግባቦት የጠራና የቀለጠፈ ይሆን ዘንድ ቃላት ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ምሁራና ከሰነዘሩት ሀሳቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡

Wallance (1982) በቋንቋ ትምህርት ቃላት ያላቸው ቁልፍ ሚና እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህም፤ በንግግር ወቅት ትክክለኛውን አነጋገር መጠቀም፤ የቃላትን ቀጥተኛ (ጥሬ ትርጉም ወይም መዝገበቃላዊ ፍች) እና ፍካሬያዊ (የቃላት ተጨማሪ ፍች ወይም ሚስጥራዊ ፍች) እዲያውቁ የስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቃላትን በተገቢው ቁስና ፅንሰ ሀሳብ ጋር ማዋሀድ እንዲችሉ ከማድረጉም በላይ ቃላትን በተገቢው ሰዋሰዋዊ ቅርፅም መዋቅር እንዲጠቀሙባቸው፤የቃላትን ትክክለኛ ዘይቤያዊ አነጋገር፣ ፈሊጣዊ፣ ቅኔያዊ፣ ወዘተ አጠቃቀም፤ቃላትን የንግግር ወይም የፅህፈት ቅርፅ ለመየት፤የቃላትን ተገቢውንና መደበኛውን አነጋገርና የአፃፃፍ ስርዓት ጠብቀው እንዲገለገሉ ወይም እንዲጠቀሙ ያግዛቸዋል፡፡

ከላይ ከጠቀሱት ነጥቦች መረዳት እንደሚቻለው የቃላትን ትርጉም ከመገንዘብ በተጨማሪ ቃላት እውቀት ወሳኝ መሆኑንና ቃላት ሌሎች የቋንቋ ዘርፎችን ለማቀላቀጠፍ የማይተካ ሚና የሚጫወቱ መሆኑን ነው፡፡ Rechards እና Rogers (2001) አገላለፅ፣ በቋንቋ ትምህርት ለተግባቦት እንደመሰረት ድንጋይ የሚሆኑት ቃላት ናቸው፡፡ በመዋቅር ውስጥም የትኛው ትክክለኛ ሰዋሰው እንደሆነ እና እንዳልሆነ ቃላት መልስ ይሰጣሉ፡፡ Lewis (1993) ስለ ቃላት አስፈላጊነት ሲያብራራ፣ ከሰዋሰው ይልቅ ቃላት ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ የገለጹ ሲሆን ምክንያታቸውም ስነ አገባብ ቃላት አገልግሎት በሚሰጡበት ሁኔታ ለማዋቀር የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ተጠይቃዊ ግንኙነት የሚመለከተው ቃላት ከሰዋሰው በተሻለ መልኩ እስፈላጊና ወሳኝ መሆናቸውን ነው፡፡

Picklski እና Temleton (2004) እንደጠቆሙት፣ ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ኑሯቸው የለውጡ ተሳታፊ እንዲሆኑና ከሌሎች በልጠው ለመገኘት የቃላት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው። ምክኒያቱም ተማሪዎች በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ግንኙነት የበዛበትና በውድድር አለም ውስጥ አሸንፈው እንዲኖሩ እና አቅም እንዲፈጥሩ የቃላት እውቀት እና ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል።

## 2.3 በቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

ETP (1994) እንደገለፁት፣ ለትምህርት ጥራት መቀነስ በዋናነት ከሚጠቀሱት ችግሮች መካከል በቂ የሆነ የመምህራን ስልጠና አለመኖር፣ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ የመምህሩ የልምድ ማነስ፣ የመጽሀፍትንና የተለያዩ የመማሪያ መሳሪያዎች እጥረት የሚሉት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ችግሮች በቃላት ትምህርት ሂደት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራሉ።

### 2.3.1 ከመምህራንና ከተማሪዎች ተነሳሽነት አኳያ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

የቃላት ትምህርት በተሳለቀ መልኩ እንዲቀጥል ወይም እንዳይቀጥል መምህራን ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች በሚቀርብበት ጊዜ በመምህራን በኩል የታዩ ክፍተቶች ወይም ችግሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ፤ ለመሳሌ የአመለካከት ችግር፣ የአቅም ማነስ፣ በቂ ዝግጅት አለመኖር ወዘተ. ለቃላት ትምህርት መማር ማስተማር አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ለቃላት ትምህርት የተማሪው ተሳትፎ የላቀ አስተዋፅኦ እንዳለው አያጠያይቅም። ለመሳሌ የተማሪዎች የአመለካከት ችግር፣ የተማሪዎች ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት፣ የተማሪዎች ግዴለሽነት መሆን፣ አካባቢያዊ ተፅዕኖ ወዘተ ናቸው።

Brown (1994) እንደሚያስረዱት፣ በአንድ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸው ግብረመልስ አነስተኛ እንዲሆን፣ ተማርዎች በክፍል ውስጥ በሰፊው እየተሳተፉ የሚማሩበት አጋጣሚ እንዲመነምን እና መምህራንም የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት፣ ችሎታ፣ ተሳትፎና ዳራውን እንዳያውቁና እንዳይከታተሉ ስለሚያደርግ አሉታዊ ተፅዕኖው ከፍተኛ ነው።

### 2.3.2 የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት በተመለከተ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

የማስተማሪያ መሳሪያዎች ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ለቃላት ትምህርት አቀራረብ ከመምህራን ቀጥሎ እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ እንደ Nasar (1979) አገላለፅ፣ አንድ ተማሪ የተማረውን አደምጦ ከተማረው በበለጠ ሁኔታ በአዕምሮው ቀርፆ ይይዛል፡፡ በመሆኑም የማስተማሪያ መሳሪያዎች የቃላትን ትምህርት ለማስተማር ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሆነ ነው፡፡ Pratt (1994) እንዳስረዱት፣ በቋንቋ ትምህርት በተለይም የቃላት ትምህርት የተሳካ ትግበራ እንዳይኖር ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉት ነገሮች መካከል ተገቢና ብቃት ያላቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች አቅርቦት አለመሟላት እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

## 2.4 ቃላትን ቀጥተኛ የማስተማር ብልሃቶች

Oxford (1990) እንዳስረዱት፣ ቀጥተኛ ብልሃቶች ተማሪዎች በቀጥታ በቋንቋ ትምህርት ሂደት እየተሳተፉ የተለያየ ተግባራትን እያከናወኑ ተተኳሪውን ቋንቋ ቃላትን እንዲማሩ በቀጥታ የሚያግዟቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ብልሃቶች የትውስታ ብልሃቶችና አእምሯዊ ብልሃቶች ናቸው፡፡

### 2.4.1 የትውስታ ብልሃቶች

እንደ Seal (1991) እንደገለጹት፣ አዳዲስ ቃላትን በማቅረብ ማስተማር ብቻውን ውጤታማ አያደርግም፡፡ ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት በየትኛውም ቦታ አስታውሰው መጠቀም እንዲችሉ መታገዝ አለባቸው፡፡ ስለሆነም መምህራን የቃላት ትምህርት ሲያስተምሩ ያስተማሯቸውን ቃላት በተማሪዎች አዕምሮ ሰርጸው እንዲቀሩ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ Ur (1996) እንደገለጹት፣ አዳዲስ ቃላትን በማቅረብ ማስተማር ብቻውን ውጤታማ አያደርግም፡፡ ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት በየትኛውም ቦታ አስታውሰው መጠቀም እንዲችሉ መታገዝ አለባቸው፡፡ ስለሆነም መምህራን የቃላት ትምህርት ሲያስተምሩ ያስተማሯቸውን ቃላት በተማሪዎች አእምሮ ሰርጸው እንዲቀሩ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ Ur (1996) እንደገለጹት፣ አንድን ቃል ከሌላው በተለየ ስልት እንድናስታውስ የሚያደርጉን የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህም የቃላት ባህሪ፣ የተማርንበት መንገድ፣እና የተማርንበት ዘዴ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ቃላትን በአምሮው መዝግቦ በመያዝና ረጅም ጊዜ ትውስታ በመፈጠር በአስፈላጊው ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚረዱ ብልሀቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990)፣ ተማሪዎች አንዱ **መሰረታዊ ችግር** በአንድ ወቀት የተማሯቸውን ቃላት ወይም አገላለፆች በሌላ ጊዜ መርሳት ነው፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ ለተለያዩ ጉዳዮች በጣም የሚጠቅሟቸውን ልዩ ልዩ የቃላት አይነቶችንና አገላለፆችን አስታውሰው መጠቀም አለመቻል ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ Oxford (1990) እንዳስረዱት፣ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢ የሆነው የትውሰወታ ብልሃት በአእምሮ ውስጥ ምስል የመፍጠር ብልሃት ሲሆን የሚተሉትን ዝርዝር ብልሀቶች በውስጡ ያካትታል፡፡

**መቦደን**፤ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ቃላት በአንድነት በመቦደን ከአዕምሮ ጋር በማያያዝ የማመቻቸት ብልሃት ነው፡፡ አንድ ጊዜ የተማሯቸውን አዳዲስ ቃላት በቀላሉ አስታውሶ ለመጠቀም ለምሳሌ ከአንድ ጉዳይ ጋር የተያያዙ ቃላትን በአንድ ላይ፣ በቃል ክፍላቸው ለምሳሌ ስሞችን ወይም ግሶችን በአንድ ላይ፣ በፍቺ ተመሳሳይ የሆኑትን ለምሳሌ ድቡልቡል፣ ክብ፣ ወይም በተቃራኒያቸው ሸካራ፣ ለስላሳ፣ በአንድ ላይ መቦደን፣ አንድ ሰው ስለአንድ ነገር ያለውን ስሜት ለመግለጽ የሚያገለግሉ ቃላትን በአንድ ላይ ለምሳሌ መጥላት፣ መውደድ ወዘተ፣ በሰዋስዋዊ አገባባቸው ለምሳሌ፤ አንተ፣አንቺ፣እሱ፣እሷ፣እነሱ ወዘተ. ትርጉም ባለው መንገድ በማደራጀት ማስተማር ነው፡፡

.ትርጉም ባለው መንገድ በማደራጀት ከአእምሮ ጋር በማያያዝ ለትውስታ መማቻቸት ፡፡ መየቦደን ብልሃት Nation (2001)፣ Schmitt (1997) እና Cohen (1990)ም ከትውስታ ብልሃቶች ተማሪዎች በአንድ ወቅት የተማሩትን ቃል በአስፈላጊ ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚረዳቸው በጣም መሰረታዊ ብልሃት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

**ሥነፍቻዊ** ካርታ፤የትርጉም ግንኙነት ያላቸውን ውስን ቃላት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ሊያሳይ በሚችል ስዕል ላይ በመደርደር ማሳየት በአዕምሮ ውስጥ ትውስታን መፍጠር፡፡ በሌላ አገላለጽ ዋናውን ቃል መሃል ላይ በማስቀመጥ ከዋናው ቃል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቃላት ከዋናው ቃል ጋር በቀስት በማገናኘት ቃላቱን ለረጅም ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚያስችል ብልሃት ነው፡፡ ይህ ብልሃት የተወሰኑ የቃላት ስብስቦች እንዴት እርስ በርስ ግንኙነት እንዳላቸው በግልጽ ለመረዳት ስለ ሚያስችልና አዳዲስ ቃላትን ለረጅም ጊዜ በአእምሮ ውስጥ መዝግቦ በማቆየት በአስፈላጊ ጊዜ አስታውሰው ለመጠቀም

ውጤታማ በመሆኑ በአብዛኛው በስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች ተግባራዊ ይደረጋል (Schmitt፣ 1997፤ Brown እና Perry፣ 1991)፡፡

**ክለሳማካሄድ፤** በአንድ ወቅት የተማሩትን ቃላት የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር በሚል ዓላማ በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ የመከለስ ብልሃት ነው፡

## 2.4.2 አእምሯዊ ብልሃቶች

ተማሪው የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት በቀጥታ አእምሮውን በመጠቀም ተረድቶና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው፡፡ Rubin (1987)ም እንዳስገነዘቡት አእምሯዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ሲማሩ በቀጥታ አእምሯቸውን በመጠቀም የሚተገብሯቸው የአሰራር መንገዶች፣ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ወይም ችግር ማቅለያዎች ናቸው፡፡ ተማሪው በተተኳሪው ቋንቋ ቃላት ተግባራት ላይ በቀጥታ የሚጠቀምባቸው መሰረታዊ አእምሯዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ምንጭ መጠቀም፤** በተተኳሪው ቋንቋ በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያጋጥሙ አመለማመድ፤ የንበት፣ የመጥበቅና መላላት ወዘተ ልምምድ ማድረግ፤ በአንድ አይነት ወይም በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ ነገር ግን በንበት በሚለያዩ ቃላት ላይ ልምምድ ማድረግ፣ የቃላት አመሰራረትን በተደጋጋሚ የተለያዩ መልመጃዎችን በመስራት ልምምድ በማድረግ፣ የቃል ክፍሎችን በመለየት ልምምድ በማድረግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ይህ ብልሃት ከአእምሯዊ ብልሃቶች በጣም መሰረታዊ ብልሃት ነው (Oxford፣1990)፡፡

አዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለማወቅ በንግግርና በጽሑፍ መልዕክት ለማስተላለፍ የቃላት አውቀታቸውን ለማዳበር በቋንቋው የተጻፉ የታተሙ ለምሳሌ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ልቦለድ፣ መማሪያ መጽሐፍ ወዘተ. በየትኛውም ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቋንቋው የተጻፉ ጽሑፎችን በማንበብ፣ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የመሳሰሉ ምንጮችን በመጠቀም የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ፍቺና አጠቃቀም ለመረዳት የሚያገለግል ብልሃትነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የአዳዲስ ቃላትን አውዳዊ አጠቃቀም ለመረዳት በቋንቋው የተጻፉ የተለያዩ ምንጮችን የመጠቀም ብልሃት ነው፡፡ እነዚህ ምንጮች ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ በቀጥታ በአውድ ውስጥ እንዲማሩና ስለተተኳሪው ቋንቋ ጠቃሚ ዳራዊ መረጃ ስለሚሰጡ ተማሪዎች ቃላቱን

በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ስለሚረዷቸው በአብዛኛው በስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ (Gu እና Johnson፣1996፤ Nation፣ 2001)::

***መደጋገም***፤ አዳዲድስ ቃላትን ደጋድሞ መፃፍና ደጋግሞ ማለት ( የተለያዩ ቃላት በፁሁፍ ወይም በንግግር ተግባቦት ሂደት ደጋግሞ መጠቀም)፣ ቃላቱን ለብዙ ጊዜ ማዳመጥ፣ በአእምሮው ውስጥ ማመላለስና በተተኳሪው ቋንቋ የመገልገል ችሎታ ያላቸውን ሰዎች አጠቃቀም በመውሰድ የቃላት ችሎታን ለማዳበር የሚያገለግል ብልሃት ነው፡፡

**እንደገና ማቀናበር**፤ ቀደም ሲል የተማሯቸውን ቃላት በአዲስ መልክ በማቀናጀት ትርጉም የሚሰጡ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ ደጋግሞ መልመጃዎችን መስራት፡፡

***ማስታወሻ መያዝ***፤ በተለያየ አጋጣሚ የሚያገኙትን የአዳዲስ ቃላትን ፍቺና አጠቃቀም በአንድ የቃላት ማስታወሻ ደብተር መዝግቦ በመያዝ ማጥናትና መለማመድ፣ በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን መዝግቦ በመያዝ ፍቺና አጠቃቀማቸውን ምንጭ በመፈለግ የቃላት ችሎታን ለማዳበር የሚጠቀሙበት ብልሃት ነው፡፡ ተማሪዎች ማስታወሻ ሲይዙ አዳዲስ ቃላትን አቻ ፍቺ በመፈለግ ማስታወሻ መያዝ፣ የቃላቱን ተመሰሳይ፣ ተቃራኒ፣ ፍካሪያዊ ፍቺ፣ የቃል ክፍላቸውንና የቃላቱን ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ወይም መዝገበቃላት ሳይመለከቱ ቃላቱ በራስ ቋንቋ ያለውን አቻ ፍቺ ፈልጎ መረዳት ወዘተ.ያካትታል፡፡

ማሸጋገር፤ ቀደም ሲል በሌላ ቋንቋ የቀሰሙትን የቃላት ዕውቀት የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት ፍቺ ለመረዳት በቀጥታ ተግባራዊ የማድረግ ብልሃትነው፤

***መተርጎም***፤የተተኳሪውን ቋንቋ በመተርጎም የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት መጠቀም::

**ልሳነዋህድ መዝገበቃላትመጠቀም**፤ መዝገበቃላት መጠቀም አዳዲስ ቃላት ለማስተማር በጣም ጠቃሚና ተጨባጭ ምንጭ ነው፡፡ ልሳነዋህድ ወይም በቋንቋው የተጻፈው መዝገበ ቃላ የቃሉን ፍቺ፣ በቃላቱ የተመሰረቱ ዐረፍተነገሮችን ምሳሌ፣ ተመሳሳይ፣ ተቃራኒ ፍቺና የቃል ክፍሉን ወይም ሌሎች ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ስለሚያካትት የቃላትን መደበኛ ፍቺና አጠቃቀም ለይተው እንዲያውቁ ስለሚረዳቸው በተለይ ቋንቋውን በጽሑፋዊ አፍልቆት ለመጠቀም ከመዝገበቃላት የበለጠ በጣም ጠቃሚ ብልሃት ነው (Oxford፣ 1990)፡፡

በርካታ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት አብዛኞቹ ተማሪዎች ሁል ጊዜ በመዝገ በቃላት መግቢያ የቀረበውን አጠቃቀም አያነቡትም ወይም ትኩረት አይሰጡትም። ምንናልባትም ለተማሪዎች የቃላት እውቀት ማነስ አንዱ ምክኒያት የቃላት እውቀትን ሊያዳብሩ የሚችሉ ምንጮችን በተገቢው መንገድ መጠቀም አለመቻል ሊሆን ይችላል። በተለይም ይህ ችግር ልሳነዋህድ መዝገበቃላት አለመጠቀም ሂደት በስፋት ይስተዋላል (Sokmen፣1997)።

በተጨማሪም Scholfield (1997) ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት ከልሳነክልኤ መዝገበቃላት የበለጠ ጥረት ስለሚጠይቅ ጥልቅ አእምሯዊ ሂደት እንዲከሰትና ቃላቱን በረጅም ጊዜ ትውስታ መዝግቦ ለማቆየት የተሻለ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች በአግባቡ መጠቀም ስለማይችሉ በልሳነዋህድ መዝገበቃላት የቀረቡ መረጃዎችን ለምሳሌ ምልክቶች (symbols)፣ አጽህሮተቃላት፣ የቃሉን የቃል ክፍል፣ የቃሉን ግንድ፣ በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ቃላትን መፈለግንና የቃላቱን ፍቺ ለማሳየት የቀረቡ ምሳሌዎችን ወዘተ በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ማስተማርና ማለማመድ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

Alseweed (2000) ም በአረብኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች በመዝገበ ቃላት ባግባቡ እንዲጠቀሙ የመዝገበቃላት የመጠቀም ብልሃት አጠቃቀምን በክፍል ውስጥ ማስተማርና ማለማመድ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል። Sokmen (1997) ልሳነዋህድ መዝገበቃላት ሰዎች ስለ ቋንቋው ለማወቅ መረጃ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት ተገቢ መሳሪያ ነው።

## 2.5 ኢ-ቀጥተኛ ቃላትን ማስተማር ብልሃቶች

Oxford (1990) በዚህ ክፍል የሚመደቡ ብልሃቶች ቀጥተኛ ባልሆነ/በተዘዋዋሪ/ መንገድ ለቃላት እውቀት መዳበር የሚያግዙ ናቸው። የተማሪውን ዘወትር የተተኳሪውን ቋንቋ ተግባራት በቀጥታ መስራትን የሚጠይቁ አይደሉም። ነገር ግን በተለያዩ መንገዶች ለቃላት ትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የትምህርታቸውን ሂደት ለመምራትና ለማመቻቸት የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው። በዚህ ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ንዑስ ብልሃቶችም (ልዕለ አእምሯዊ፣ ስሜት-ነኪ ቁጥጥርና ማህበራዊ ብልሃቶች) ናቸው።

### 2.5.1 ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሀቶች

ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ከተማሪው ስሜት፣ ዝንባሌና መነቃቃት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንዲሁም አሉታዊ ዝንባሌ ለመቋቋም (ለመቆጣጠር) የሚጠቀማቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ቃላትን በሚማሩበት ወቅት የሚያጋጥማቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግር በብቃት ይቋቋማሉ፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ ዋናዋና ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፡

**ኀላፊነትን መቀበል**፤ በትምህርቱ ሂደት መሳሳት እንደሚኖር በማመን ከባድ የቃላት ተግባራትን ስሜትን ተቆጣጥሮ ለማከናወን ኀላፊነትን ተቀብሎ መሳተፍ ለምሳሌ በሐሳብ ልውውጥ ሂደት ተገቢ ቃላትን መጠቀም ስለማልችል እሳሳታለሁ የሚል ስጋትን አስወግዶ ያለ ፍርሃት በንቃት መሳተፍ፤

**ራስን መሸለም**፤ በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ ራስን መሸለም፤ ለምሳሌ በቃላት ፈተና ጥሩ ውጤት ሲያገኙ ራስን ማድነቅ፤

**አዎንታዊ ገለፃ መስጠት**፤ ለራስ እእውቀት ጥሩ ግምትና አዎንታዊ መግለጫ መስጠት፣ በተለይም ከባድ የቃላት ተግባራትን ከመስራት በፊት የራስን ችሎታ ማድነቅ

### 2.5.2 ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች

የልእለ አእምሯዊ ብልሃቶች ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት፣ የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመቆጣጠር፣ በአጠቃላይ ያሳየውን ለውጥና የትምህርቱን ውጤት ለመገምገም የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች ናቸው (Oxford, 1990)፡፡ O'malley & Chamot (1990) እንዳስገነዘቡት የልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች የመማር አቅጣጫቸውን ያልለዩ፣ የመማር አቅድ የሌላቸው፣ እድገታቸውን የማይቆጣጠሩ፣ ስኬታቸውን የማይገመገሙና ቀጣይ የመማር አቅጣጫቸውን የማያውቁ ናቸው፡፡በልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች በተማሪው የሚከናወኑ ተግባራትም፤

**የልምምድ አጋጣሚዎችን ለማግኘት መጣር፤** ለቃላት ትምህርት አመቺ ተፈጥሮአዊ አካባቢ (ሁኔታ) መፍጠር፣ ለቃላት ትምህርት ኘሮግራም ማዘጋጀት፤

**ትኩረት መስጠት፤** ለቃላት ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ለማስተማር አስቀድሞ መወሰንና በራስ ግምገማ ተገቢ የቃላት ተግባራትን መርጦ ትኩረት ለመስጠት፡፡

**ማቀድ፤** ለቃላት ትምህርት የራስን ግብና አላማ ማስቀመጥ፣ ከቃላት ትምህርቱ ምን እንደሚጠብቅ /እንደምትጠብቅ አስቀድሞ የማቀድ ብልሃት ነው፡

**ራስን መቆጣጠር፤** ቃላትን በትክክለኛ ወይም በተሳሳተ መንገድ እየተማረ መሆኑንና የብልሃት አጠቃቀሙን በራስ በመከታተል በቃላት ትምህርት ሂደት የራስን ስህተት በራስ መለየት፤

**ራስን መገምገም፤** የቃላት ትምህርቱን ውጤት በመፈተሽ ካለፈው የበለጠ መሻሻል (ለውጥ) ማሳየት አለማሳየቱን ራስን በራስ የመገምገም ወይም ተማሪዎች የቃላት መማር ሂደታቸውን የሚገመግሙበት ብልሃት ነው፡፡

## 2.5.3 ማህበራዊ ብልሃቶች

Oxford (1990) እንዳስረዱት እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ከክፍል ጓደኞቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር ቃላትን እንዲማር የሚረዱት ብልሃቶች ናቸው፡፡ ቋንቋን ለማስተማር የሌላ ሰው ተሳትፎ አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ ተማሪዎችም ለቃላት ትምህርታቸው ውጤታማነት በጋራ ሊሰሩ ይገባል፡፡ ስለሆነም ማህበራዊ የማስተማር ብልሃቶች ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተጋገዙ፣ ግልፅ ያልሆነላቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን እንግዳ ቃላት ትርጉም መምህራንን ወይም ሌሎች ሰዎችን እየጠየቁ እንዲማሩ የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡በተማሪዎች የሚተገበሩ ማኀበራዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

**በቋንቋው የመጠቀም ብቃት ካላቸው ሰዎች ጋር መተባበር፤** ተተኳሪውን ቋንቋ በብቃት ከሚናገሩ ሰዎች ጋር ህብረት(ጓደኝነት) በመመስረት የቃላት ዕውቀትን የማሻሻል ብልሃት ነው፡፡

**ከብጤ ጋር መተጋገዝ፦** ለጋራ አላማ ከክፍል ጓደኛ ጋር በቡድን ወይም በጥንድ በመስራት (ማጥናት) የቃላቱን ፍቺ በመለማመድ የቃላት ዕውቀትን የማሻሻል ብልሃትነው፡፡

**መጠየቅ፤** የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም መምህራንን፣ የክፍል ጓደኛን ወይም ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ፣ ወይም ስህተትን ማስተካከያ የእርምት ትብብር በመጠየቅ የቃላት እውቀትን የማዳበር ብልሃት ነው፡፡

## 2.6 የሃሳብ ድር ብልሃት

### 2.6.1 የሃሳብ ድር ብልሃት ምንነት

የሃሳብ ድር ብልሃት የአእምሮ ካርታ የሆነ ቃላትን ሰንሰለታዊ በሆነ መንገድ በማሳየት የሚያስተምር ብልሃት ሲሆን፤ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የማሰብ ደረጃን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያጎለብት ቃላት የማስተማር ብልሃት ነው (Bornay፣ 2011)፡፡ ይህም Rosenbuom በተባለ የመስኩ ባለሙያ የተነደፈ (የቃላት ችሎታ በማሳደግ የቃላትን ትርጉም፣ ተመሳሳይና ተቀራኒውን፣ አውዳዊ ፍቺ፣ አገባባዊ ፍቺ፣ ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ በተለያዩ ቴክሰቶች ማለትም በልቦለድ፣ ኢ-ልቦለድና ሌሎች ታሪኮች ውስጥ ንባቦች በመረዳት አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ መትርጓም የሚያስችል ብልሃት ነው፡፡


ይህ ቃላት የማስተማር ብልሃት ተማሪዎች በተለያዩ ቅረፅ ያለውን ስዕል በመሳልና እያንዳንዳቸው ከላይ ወደ ታች መደርደር፤ በስዕሉ ውስጥ አዳዲስ ቃል ከአነበቡት ንባብ በመውሰድ እንዲፅፉ ማድረግ፤ በስዕሉ ውስጥ እንዲመዘግቡ የተደረገውን አዳዲስ ቃል የቃላቱን ፍቺ ጭምር እንዲፅፉ ማደረግ፤ የተገኘውን አዳዲስ ቃላት ከመዘገበ ቃላት ወይም ከሙዳዬ ቃላት የቃሉን ትርጉም እንዲፅፉና እንዲሁም ያገኙትን የቃላት ፍቺ ከራሳቸው ጋር እንዲያነፃፅሩ በማድረግ ለእያንዳንዱ የቃላቱ ተመሳሳይ ፍቺ፣ ተቀራኒ ፍቺ፣ አገባባዊ ፍቺ፣ አውዳዊ ፍቺ እንዲሁም እማሬያዊን ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡

በሃብ ድር ብልሃት ተማሪዎችን ቃላትን ማስተማር የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ይህም ተማሪዎች በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ወይም በሁሉም ክፍል በተነሳሽነት ንቁ በሆነ ቃላት በአእምሯቸው እንዲሰረፅ ያደርጋል፤የቃላት ትርጉምን በጥልቀትና በቀላሉ ለመረዳት ይጠቅማል፤ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥና በቀለም ትምህርታቸው ንቁና ታታሪ እንዲሆኑ ያደረጋል፤ ተማሪዎች የተለያዩ መረጃን እንዲያነፃፅሩና እንዲያወዳዲሩ ይረዳቸዋል::

እንዲሁም ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ፣ ተቀራኒ ፍቺ፣ አገባባዊና አውዳዊ ትርጉም እንዲሁም እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲረዱ ማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ስለዚህ ይህንን ቃላት የማስተማር ብልሃት ለብዙ ጊዜ ደጋግሞ በመተግበር ሁሉንም የቃላት ፍቺ እንዲረዱ ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ከተቻለ ግራፎቹ (ስዕሎች) የተደራጁ ቢሆን የተሻለ ይሆናል፡፡

የሃሳብ ድር ብልሃት ቃላትን የማስተማር ዘዴ ፅንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ (ስእላዊ) መግለጫ ምሳሌ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ስዕል 2.1




### 2.6.2 የሃሳብ ድር ብልሃት የክፍል ውስጥ አቀራረብ

የቃላት ማስተማር ስልጠና በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የሚመራበት ቅደም ተከተላዊ ማዕቀፍ አለው፡፡ ብልሃቶችን ማሰልጠን የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸው የአቀራረብ ቅደም ተከተላዊ ሲያቀርቡ ይስተዋላል፡፡ Jones እና ሌሎች (1987) እና Omalley & Chamot (1990) የተለያ ሙሁራን በተግባር ላይ የዋሏቸውን የብልሃት ስልጠና አቀራረብ ቅደም ተከተሎችን አስፍረዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ቋንቋን ጨምሮ ለሌሎች ትምህርቶችም ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸው William & Burden (1997) እንዲሁም የቃላት ማስተማር ብልሀቶችን ለማቅረብ ተግባራዊ የተደረገው Chamot (2005) የብልሃቶች ትምህርት አቀራረብ ቅድም ተከተል ይገኝበታል፡፡ ምሁራኑ ያቀረቡት የቃላት ማስተማር ብልሃቶች ስልጠና ቅደም ተከተላዊ ማዕቀፍ ተጠቃሎ ሲታይ ከታች የቀረቡትን ደረጃዎች ይከተላል፡፡

1. ታላሚውን ብልሃት ማስተዋወቅ፤ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች አዲስ ከሚቀርበው የቃላት ማስተማር ብልሃት ምንነትና ጠቀሜታ ጋር የሚተዋወቁበት ስለሆነ እንዲማሩ ከተፈለገው የቃላት ማስተማር ብልሃት አጠቃላይ ገጽታዎች ጋር የሚተዋወቁበትና ብልሃቱን ለመተግበር የሚዘጋጁበት በመሆኑ የቃላት ማስተማር ብልሃቶቹን መቼ፣ እንዴትና ለምን እንደሚጠቀሙባቸው ሰፊ ማብራሪያ በመምህራን ይሰጣል።

2. ሞዴል ሆኖ ማሳየት፤ ይህ ደረጃ መምህሩ በደረጃ አንድ ለተማሪዎች ያስተዋወቀው ብልሃት እንዴት በተግባር ላይ እንደሚውል እየሰራ የሚያሳይበት፣ ተማሪዎቹ ከመምህሩ የቀረበላቸውን ተግባራዊ ትውውቅ መሰረት አድርገው የብልሃቱን አተገባበር የሚለማመዱበት ነው። በመሆኑም በማስተማር ሂደቱ መምህሩ ሞዴል በመሆን የቀረበውን የብልሃት አጠቃቀም ተግባራቱን እየሰራ ለተማሪዎች ያሳያል።

3. ብልሃቶቹን በትብብር መተግበር፤በዚህ ድጃ መምህራንና ተማሪዎች በጋራ ብልሃቶችን በመጠቀም የቃላት ተግባራትን ይሰራሉ። እንዲሁም ተማሪዎች የራሳቸውን የብልሃት አጠቃቀም የመገምገም ችሎታ እንዲያዳብሩ ብለሃቶቹን በመተግበር ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮችና የወሰዷቸውን መፍትሄዎች የተማሩትን ብልሃት ምን ያህል እንደተረዱት ለመገምገም በብልሃት አጠቃቀማቸው ላይ ከመምህራን ጋር በመወያየት ብልሃቶቹን ወደፊት ለመተግበር ያላቸውን ፍላጎት የሚገልጹበት ሁኔታም ይመቻቻል።

4. የብልሃቶቹን አተገባበር መምራት፤ የተማሪዎቹን የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር ተማሪዎች በደረጃ አንድ የቃላት ማስተማር ብልሃት ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ ከተገለጸላቸውና በደረጃ ሁለት በመምህሩ ሞዴልነት (ምሪት)ና በደረጃ ሶስት ከመምህሩ ጋር በጋራ የተለማመዷቸውን ብልሃቶች በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው የተለያዩ ተግባራትን እየሰሩ በራሳቸው በብልሃቱ አተገባበር በጋራ እንዲለማመዱ ይደረጋል። በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ብልሃቶቹን በሚተገብሩበት ጊዜ እየተከታተሉ መምራት (ድጋፍ መስጠት) ያድፈልጋል። የማለማመዱ ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሃላፊነቱን ለተማሪዎች በመስጠት ራሳቸውን ችለው ከተማሯቸው ብልሃቶ እንደየ አግባብነታቸው እየመረጡ እንዲጠቀሙ ማድረግ ይገባል።

## 2.7 የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት

እንደ አእምሯዊ የቋንቋ ማስተማር ንድፈ ሀሳብ አራማጆች እይታ የቋንቋ ማስተማር ብልሃቶች ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ ውስብስብ አእምሯዊ ክሂል ነው፡፡ አያይዘውም ቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ብልሃቶችን በተገቢው መንገድ የሚጠቀሙ ከሆነ በትምህርቱ ሂደት የሚገጥማቸውን ችግር በራሳቸው በማቅለል ቋንቋውን አቀለቀጥፈው መጠቀም ይችላሉ (Mitchell፣ Myles፣ & Marsden፣ 2013)፡፡
ስለሆነም በአእምሯዊ የቋንቋ ማስተማር ንድፈ ሀሳብ ውስጥ የቋንቋ ማስተማር ብልሃቶች በጣም መሰረታዊ ናቸው፡፡ በማህበራዊ የቋንቋ ማስተማር ንድፈ ሃሳብ እይታም ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም እንደ ከፍተኛ የአእምሮ ስራ ይቆጠራል፣ ለምሳሌ መረጃን መተንተን፣ ያገኙትን መረጃ ከቀደመ እውቀት ጋር ማያያዝ፣ ማቀድና መገምገም ወዘተ. ብልሃቶችን የመጠቀም ሁኔታ ከፍተኛ የአእምሮ ስራ የሚጠይቅ በመሆኑ ተማሪዎች በማህበረ ባህላዊ አውድ ውስጥ የተሻለ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ድጋፍ የሚያዳብሩበት ነው (Oxford & Schraman፣ 2007)::

በዚህም የቃላት ማስተማር ብልሃቶችን በሽግግራዊ የብልሀት ትምህርት ሞዴል ማስተማር ለግንዛቤ ማደግ ማህበራዊ መስተጋብር መሰረታዊ ሚና አለው በሚለው በVygotsky (1978) የማህበራዊ ግንባታ ንድፈሀሳብ (Sosial Constructivist Theory) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች እይታ መሰረትም አንድ ሰው በግሉ ከሚማር ይልቅ የተሻለ እውቀት፣ ግንዛቤና ክህሎት ባላቸው ሰዎች እየታገዘ ቢማር የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

## 2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚማሩ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮች የተደረጉ ናቸው፡፡ Bryant እና ሌሎች (2003)፣ Jitendra፣ Fdward፣ Sacks Jacobson (2004) ጥናቶች መካከል አንዱ የሀሳብ ድር ወይም ግራፊክ አደረጃጀት በመባል ይታወቃል፡፡ ይህም የቃላትን ሥነ-ፍች ለማወቅ የሃሳብ ድር መዋቅር ምንጭ በመሆን አገልሏቸዋል Jitendra እና ሌሎች (2004)፡፡ የቃላት ሥነ-ፍች አወቃቀር ተግባር የሃሳብ ድርን ለመማር እንከን ላለባቸው ተማሪዎች አዎንታዊ አስተዋጥኦ እንዳለው

አመልክቷል (Ebbers፣ Denton፣ 2008)፡፡ የመማር ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ዙሪያ ከተፃፉ የቃላት ማስተማሪያ ሥነ-ፅሁፍ ውስጥ Jitendra እና ሎሎች (2004)፣ Bos እና ጓደኞቻቸው አማካኝነት የተከናወኑ አምስት ጥናትና ምርምሮችን ለይቷል፡፡

እነዚህም ጥናቶች የሚያተኩሩት ውህደታዊ የሆነ የመገንዘብ ስልት ሲሆን በዚህ ውስጥ የሚጠቀሱት የሀሳብ ድር ጥቅም ወይም ግራፊክ አደረጃጀት (የሥነ-ፍች ካርታ፣ የሥነ-ፍች የሁኔታ ትንተና ሰንጠረዥ ወይም ስዕላዊ ዋጋ እነዚህን ከመዝገበቃላት የማስተማር አጠቃቀም ጋር በማነፃፀር የትኞቹ ለተማሪዎች በተለይም የመማር እንከን ለለባቸው የቃላት ማስተማሪያነት የበለጠ እንደሚያገለግል ተሞክሯል፡፡

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥናቶች Anders፣ Bos፣ Allen፣ እና Fillip (1984) እና Bos፣ Anders፣Fillp እና Jaffe (1989) በሁለቱ የማስተማር ዘዴዎች ተፅዕኖ ዙሪያ ጥናት ያደረጉት ሲሆን እነዚህም የስነ-ፍች ጥናት የሁኔታ ትንተና በተቃርኖ በመዝገበቃላት ቃላትን የማስተማር ዘዴ ላይ ሆኖ ጥናቱ የተደረገውም በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በመማር እንከን ያለባቸው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሁለቱ ብልሃቶች መካከል ያለውን የቃላት የማስተማር ልዩነት ለማሳየት የንባብ ይዘት ከተማሪዎች ማህበራዊ ሳይንስ መፅሀፍ ተወስዷል፡፡ በሥነ-ፍች ጥናት የሁኔታ ትንተና ላይ ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም አስቀድመው እንዲተነብዩ የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም በአዳዲስ ቃላት ዙሪያ እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡

ከዚያም ቀድመው የገመቱት ትክክል መሆኑን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ጹሁፉን ያነባሉ፡፡ በመዝገበ ቃላት ቃላትን በመማር ማስተማር ሂደት የሚማሩ ተማሪዎች የቃላትን ትርጉም በመዝገበቃላት ይማራሉ፡፡ እነዚህን ቀላት በመጠቀም አረፍተነገሮችን ይፅፋሉ፡፡ የነዚህን የሁለቱን የቃላት የማስተማር ሂደት ከተተናቀቀ በኋላ ለሁለቱም ቡድኖች ቃላትን መሰረት ያደረገ አንበቦ የመረዳት ፈተና ተሰጥቷቸው ውጤቱም ያሳየው በስነፍች ጥናት የሁኔታ ትንተና ብልሃት ቃላትን የተማሩ ተማሪዎች በመዝገበቃላት ቃላትን ከማስተማር ብልሃት በላቀ ውጤታማ መሆናቸውን ነው፡፡ ለቃላ እውቀት ብልሃቶችን ተጠቅመው ማስተማራቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤የመረጃ መስብሰቢያው፣ የክፍል ደረጃው፣የተለያዩ ብልሃቶችን ተጠቅመው ማስተማራቸው ይለያል፡፡

ሶስተኛው ጥናት ላይ Bos፣ Allen እና Scanlon (1989) የሶስቱን የቃላ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ከመዝገበቃላት ማስተማርብልሃት ጋር ያወዳደሩ ሲሆን ለመዋዳደሪያ የተጠቀሙበትም

የሥነ-ፍች ጥናት አደረጃጀት ማለትም የሀሳብ ድር፣ የስሠነ-ፍች ጥናት የሁኔታ ትንተና እና የትርጉም ወይም ያገባብ ባህሪ ትንትና ሁኔታ ነው፡፡ በስነፅሁፍ ጥናት ሁኔታና በስነፍች ጥናት ላይ የተመሰረቱ ተማሪዎች ደግሞ በቃላት መካከል ያለውን ግንኙነት መተንበይ የቻሉና የግንኙነት ሰንጠረዥንም መሙላት ችለዋል፡፡ በሥነ-ፍች ጥናት ከላይ ካየነው በተጨማሪ ተማሪዎች ከሰንጠረዡ በተሰጠው መረጃ በመጠቀም የተጓደሉ አረፍተነገሮችን ማሟላት ችለዋል፡፡ በመዝገበ ቃላት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች መዝገበ ቃሉን ባህላዊ ወይም በሰለጠነ መንገድ ተጠቅመዋል፡፡

ከሂደቱ ማጠቃለያ በኂላ የተማሪዎችን ቃላት የማወቅ ችሎታቸውን ለመመዘን ፈተናን እንዲያሟሉ ይደረጋል፡፡ ይኸውም በሰንጠረዥ ውሰጥ የተጠቀሰውን ጉዳይ ቁልፍ ሀሳቡን በመረዳት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የተገኘው ውጤትም የሚያሳየው ምንም እንኳ በሃሰብ ድር ፣ የስነፍች ጥናት የሁኔታ ትንትናና በሥነ-ፍች ጥናት ለውጦች የታዩ ቢሆንም ከመዝገበቃላት ጋር ሲነፃፃር ጠቃሚ የሚባል ለውጥ የታየው ግን ከሶስቱ በስነ-ፍች ጥናት ላይ ነው፡፡ በጠጨማሪም ከመዝገበ ቃላት አጠቃቃም ዘዴ ይልቅ በስነ-ፍች ጥናት አደረጃጀት ዘዴ ተማሪዎች ከፍተኛ አንብቦ የመረዳት ውጤት አስመዘግበዋል፡፡

በተለይም በሀሳብ ድርና በስነፍች የሁኔታ ትንተና አቀራረብ ተማሪዎች ከመዝገበለቃለት አጠቃቀም በተሻለ አንብቦ መረዳት ውጤትን አሳይተዋል፡፡ በመጨረሻም የተፃፈን ነገር ከማስታወስ አንጻር በአራቱም የማስተማር ዘዴዎች መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ በአራተኛው ጥናት Bos እና Anders (1990) የሀሳብ ድር፣ ስነ-ፍች ጥናት ሁኔታ ትንተናንና የስነ-ፍች ጥናት ከመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጋር የወዳደሩ ሲሆን በሂደቱ ያገለገሉ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ሆነው በሳይንስ ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ የመማር እንከን ያለባቸው ተማሪዎች ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት የተደረጉ ሂደቶች Bos እና ሌሎች (1989) ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ውጤቱም የሚያሳየው በሀሳብ ድር እና በስነ-ፍች ጥናት ሁኔታ ተማሪዎች የላቁ የብዙ ቃላትን በመዝገበ ቃላት የማስተማር አቀራረብ ከተሰራባቸው በተሻለ መማራቸውን አረጋግጠዋል፡፡ በተጨማሪም በሶስቱ ዘዴዎች ማለትም በሀሳብ ድር፣ በስነ-ፍች ጥናት ሁኔታና በስነ-ፍች ጥናት የአቀራረብ ዘዴ ከፍተኛ የሆነ አንብቦ የመረዳት ውጤት አሰይተዋል፡፡ ምንም እንኳ ሶስቱ የቃላትን የማስተማር አቀራረብ ዘዴዎች ተመሳሳይ አንብቦ የመረዳት

ውጤትን ያመለከቱ ቢሆንም የስነ-ፍች ጥናት ከመዝደበቃላት የማስተማር ዘዴ በታሻለ ተማሪዎች ውጤት ማሳየታቸውን አረጋግጠዋል፡፡ በመጨረሻ የስነ-ፍች ጥናት ሁኔታ ትንትና ጥናት ከመዝገበቃላት የቃላት አቅራብ በተሻለ የተፃፈን ነገር ከማስታወስ አንጻር የጎላ አስተዋፅኦ እንደነበራቸው አሳይቷል፡፡

በአምስተኛው ጥናት Bos እና Anders (1992) ስድስት ጥናቶችን ያደረጉ ሲሆን አላማውም የስነ-ፍች ጥናት አደረጃጀት ቃላትን ከመማር እና አንብቦ ከመረዳት አንጻር ያለውን ተፅዕኖ ለመፈተሽ ነበር፡፡ ስድስቱ ጥናቶች በሶስት ደረጃዎች የተደራጁ ሲሆን በእያንዳንዱ አደረጃጀት በሁለት ጥናቶች ተካተዋል፡፡ ሁለተኛ ቋንቋ የሚናገሩ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን የያዙ ሲሆን እነዚህም ተማሪዎች በማህበራዊ ስይንስ የመማር እክል ያለባቸው ናቸው፡፡ ሌላው ጥናት የያዘው የመለስተኛ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ሆኖ በሳይንስ ትምህርት የመማር ሂደት ላይ ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡

ጥናቱ በሁለቱ የመጀመሪያ ደረጃዎች አላማ ያደረገው የሀሳብ ድር፣ የስነ-ፍች ጥናት ሁኔታ ትንተናና የስነፍች ጥናት በመዝገበ ቃላት የማስተማር ሂደት ላይ የላቸውን ተፅዕኖ ማሳየት ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት የሚያሳየው ከላይ በተጠቀሱ ሶስቱ የቃላት የማስተማር ዘዴዎች በመዝገበቃላት በመጠቀም ከማስተማር ዘዴ በላይ ውጤታማ መሆናቸውን ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሚገኝ ሁለቱ ጥናቶች የተደረጉበት ምክንያት የሀሳብ ድርና የስነ-ፍች ትናት ሁኔታ የአቀራረብ ዘዴዎች ቃላትን ተግብረው በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ያላቸው ድርሻ ለማወዳደር ነው፡፡

የነዚህ የመጨረሻ ጥናቶች ውጤት የሚያሳየው የሀሳብ ድርና በስነ-ፍች ሁኔታ ትንተና የአቀራረብ ብልሃት የተማሩ አንክን ያለባቸው ተማሪዎች እንከን ከሌለባቸው ተማሪዎች ጋር በሚመጣጠን መልኩ የቃላት እውቀት እንዳላቸው የሳዩ ሲሆን ነገር ግን ልዩነቱ በቡድኑ መካከል የጎላ እንዳልሆነ አሳይቷል፡፡ ቃላትን በብልሃት ማስተማር አስተዋጽኦ እዳለው ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤ የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀምና የመማር እንከን በለባቸው ተማሪዎች ላይ የተሰራ በመሆኑ ይለያል፡፡ በተጨማሪም የመረጃ መስብሰቢያው የአንብቦ መረዳት ፈተና በመሆኑ ልዩ ደርገዋል፡፡

Fore፣ Boon፣ Lowrie (2007) ላይ የሀሳብ ድር ብልሃት የማስተማር ስልትና በመዝገበቃላት የማስተማር ብልሃት በስድስት የመማር ችግር ባለባቸው መለስተኛ ተማሪዎች

ላይ ያለው ተፅዕእኖ አጥንተዋል፡፡ Anders (1984)፣ Bos እና Allen (1989)፣ Bos እና Andres (1992)፣ Bos እና Anders (1989) ጥናት ያጠኑ ሲሆን ጥናቱም ያተኮረው ቃላትን በአውድ የማስተማር ስነዘዴ ላይ ሲሆን ይኸኛው ጥናት በተቃራኒ ቃላትን በመማር ሂደት ሀሳብ ድር ማስተማር ተፅዕኖ ምን ያህል እንደሆነ ይተነተናሉ፡፡ Hairrell (2011)፣ Rupley እና Nichols (2005) በሀሳብ ድር ብልሀት የሚጠቀሙ ሲሆን አገልግሎቱም አዳዲስ ቃላትን ትርጉም በመፈለግ፣ ትርጉም በመስጠት በቃላቱ አማካኝነት አረፍተነገር በመስራት ላይ ያተኩራል፡፡ የእያንዳንዱ የማስተማር ብልሀት ካጠናቀቁ በኋላ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማወቅ መመዘኛ የቀረበላቸው ሲሆን አላማውም የአዳዲስ ቃላት እውቀታቸውን ለመገምገም ነው፡፡

ውጤቱም የሚያሳየው አዳዲስ ቃላትን ለመማር በመዝገበቃላት የማስተማር ብልሀት ይልቅ በሀሳብ ድር በመጠቀም ቃላትን ማስተማር በሁሉም ስድስት ተማሪዎች የበለጠ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ጥናቱየሃሳብድርብልሃትን ተጠቅመው ቃላትን ማስተማራቸውና ያጠናን ስልቱ ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለመመዘን የቀረበላቸውና በስድስት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተሰራ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያል፡፡

Bos እና የእሷ ጓደኞች ቃላትን ኋላ ቀር በሆነው በመዝገበቃላት ከማስተማር ይልቅ ለሁተኛ ድረጃ ተማሪዎች ሌሎች ቃላትን የማስተማር ብልሀቶች እንዳሉ በማሳወቅ መሰረቱን ጥለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ Fore እና ሌሎች (2007) ጥናት ውጤትን ማስቀጠል ሲሆን በመዝገበቃላት አቀራረብ የማስተማር ስልትንና በሀሳብ ድር የማስተማር ብልሀትን በመጠቀም የመማር እንከን ያለባቸውን የመለስተኛ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በማስተማርና ውጤት በማወዳደር ይሆናል፡፡

Brown & Perry (1991) በሃሳብ ድር ብልሃት አዳዲስ ቃላትን በአውድ ውስጥ በመጠቀም ማስተማር የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሻሻል ያለውን አስተዋፅኦ ለመፈተሸ ተማሪዎችን በሙከራና በቁጥጥር ቡድን በመከፈል ሁለት የተለያዩ መምህራን በእጣ ናሙና በመምርጥ እንዲያስተምሩ በማድረግ ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናቱ ውጤትም የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሻሻል አስተዋፅኦ እንደለው አረጋግጠዋል፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት ሁለት ቡድኖች በተለያዩ መምህር መማራቸው በመምህር ብቃት፣ ተነሳሽነትና የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ልዩነት ምክንያት በጥናቱ ውጤት ላይ የሚመጠውን አሉታዊ ተፅዕኖ

ለመቆጣጣር አስቸጋሪ በመሆኑ ጥናቱ ክፈተት ይታይበታል፡፡ ይህ ጥናት በርዕሳቸው፣ በሙከራና በቁጥትር ቡድን በእጣ በመክፈል ማስተማራቸው ተደጋጋፊነት ያላቸው ቢሆንም፤ ይህ ጥናት በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድን ሆኖ በአንድ መምህርት ቃላትን የማስተማር ብልሃት የተከናወነ በመሆኑ ልዩነት አለው፡፡

በኢትዮጵያ በመለስተኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሀሳብ ደር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ የሚመለከቱ ባይሆኑም በቃላት ዙሪያ ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ ቀጥሎ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከቃላት ጋር ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ አጥኝዋም በአደረገችወ ዳሰሳ ወይም ፍለጋ በቃላት ላይ ያተኮሩ የሀገር ውስጥ ጥናቶች የተገኙ ሲሆን እነዚህም፤ ሲሳይ (1990)፣ በላይነሽ (2010)፣ ትንሳኤ (1988)፣ አለሚቱ (2013)፣ እሸቱ (1997)፣እና ንጋቱ (2002) ናቸው፡፡

ትንሳኤ (1988) የትንሳኤ ርዕሰ ጉዳይ የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ፈተናዎች በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት የሚለው ሲሆን ምርምሩም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ አላማም በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ውስጥ የቃላት ጥያቄዎችን ተገገቢነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ ነበር፡፡ በምርምሩ የተገኘው ውጤት ጥያቄዎቹ በአውድ ያልቀረቡ፣ አቀራረባቸው አውድን ያልተከተለ፣ ግልፅ አላማ የሚጎላቸው፣ አቀራረባቸው የትምህርቱን የማስተማር ዘዴ እና አላማ መነሻ ያላደረጉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ እና የትንሳኤ ጥናት በቃላት ትምህርት ዙሪያ የተደረጉ ምርምሮች በመሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በሰባተኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፍይዳ የሚፈትሽ በመሆኑ ከትንሳኤ (1988) ጥናት ጋር የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሲሳይ (1990) በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ ያለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት፣ የሚለው ሲሆን ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት የቀረበ ነበር፡፡ የጥናቱ አላማም የዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብን መፈተሽ ነው፡፡ በምርመሩ የተገኘው ውጤትም በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ከቃላት ትምህርት አጠቃቀም ባሻገር በትርጉማቸው ላይ የተወሰነ መሆኑን፣ አውዳዊ አቀራረብ

የሚከተልና የቃላት ትምህርት አጠቃቀም ባሻገር በትርጉማቸው ላይ የተወሰነ መሆኑን፣ አውዳዊ አቀራረብ የሚከተልና የቃላት ትምህርት አቀራረብ በአብላጫ ከአንባቦ መረዳት ጋር የተቆራኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የዚህ ምርምርና የሲሳይ ጥናት በቃላ ትምህርት ላይ ያጠኑ በመሆኑ የሚየመሳስላቸው ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በሰባተኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ሀሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እቀውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ መመርመር በመሆኑ ከሲሳይ ጥናት ጋር ይለያል፤የትምህርት አቀራረቡም በአብላጫ ከአንብቦ በረዳት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ይለያል፡፡

በላይነሽ (2010) የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፤ ጾታ ተኮር ሙከራዊ ጥናት (በዘጠነኛ ክፍል ኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች) ተተኳሪነት ሲሆን የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት የቀረበ ነበር፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ መሰልጠናቸው የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡

የጥናቱ ግኝት፣ በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ወቅት ግልጽና ቅንጅታዊ የብልሃት ትምህርት አቀራረብ ሞዴል በመጠቀም አተገባበሩን እንዲለማመዱ የቃላት ተግባራት በማቅረብ አውዳዊ ድጋፍ መስጠት የብልሃት አጠቃቀምን በማዳበር የተማሩትን ብልሃት ወደ ተመሳሳይ አዳዲስ ተግባራት አሸጋግሮ በመጠቀም የቃላት ችሎታን ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በብልሃት ተደግፎ ማስተማር ለቃላት እውቀት አስተዋጽኦ እንዳለው ማሳየቱና በቃላት ላይ መጠናቱ ከዚህ ትናት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤ በመማር ብልሃት፣ በቅንጅታዊ ብልሃት አተቃቀሙ፣ በቦታው፣በክፍል ደረጃው፣ በኦሮምኛ አፈ-ፊት ተማሪዎች ላይ መስራቱ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አለው፡፡

አለሚቱ (2013) ዕርሰ ጉዳይ የቃላት ትምህርት ይዘት ተገቢነት፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤ በኦሮሚያ ክልል በተዘጋጁ የሰባትኛ እና የስምንተኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍት ተተኳሪነት በሚል ሲሆን ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነበር፡፡ የጥናቱ አላማም በኦሮሚያ ክልል አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጁ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍት ምንም አይነት ሽፋን አልሰጠም፡፡

ይሁን እንጅ በሁለቱም መፅሀፍት የቃላት ትምህርቶች ከሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች ጋር (በተለይ ከክሂል ትምህርቶች ጋር) ተቀላቅለው ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ከቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ውስጥ የቃላት ተመሳሳይ ፍች ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ይዘት ሲሆን ተቃራኒ ፍች ደግሞ ዝቅተኛ ሽፋን የተሰጠው ይዘት ነው፡፡ የዚህ ምርምር እና የአለሚቱ ጥናት በቃላት ዙሪያና ስለ ቃላት ትምህርት ማንሳታቸው የሚያመሳስላቸው ሲሆን፣ የዚህ ጥናት ትኩረት ግን የሀሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማዳበር ያለውን ፋይዳ ለመመርመር በመሆኑ ከአለሚቱ ጥናት ጋር ይለያል፡፡

እሸቱ (1997) የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ከዘመናዊ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ያለውን ተገቢነት ለመፈተሽ ያጠና ሲሆን፣ ከዚህ ጥናት ጋር በቃላት ዙሪያ ማጥናቱ ቢመሳሰልም በጥናቱ ብልሀትና በቦታው ይለያል፡፡

የንጋቱ (2000) ጥናት የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም በመፈተሽ ላይ ያተኮረና ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት የሃሳብድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡

# ምእራፍ ሶስት፤ የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት አላማ የሃሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ይህን አላማ ለማሳካትም ጥናቱ በፍትነት መሰል Quasi-Expermental) ስልት ላይ የተመሰረተ የሁለት ቡድኖች (የቁጥትርና የፍትነት) ቅድመትምህርት ፈተናና ድህረትምህርት ፈተና (quasi-experimental pretest-posttest comparison group) የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የፍትነቱ ቡድኑ ተሳታፊዎች በሀሳብ ድር ብልሃት አማካኝነት፤የቁጥጥሩ ቡድን ተሳታፊዎች ደግሞ በመምህር መምሪያውና በተማሪ መጽሀፍ አማካይነት ቃላትን ተምረዋል፡፡

ሁሉም ቡድኖች የቃላት ትምህርቱን ለተመሳሳይ ክፍለጊዜያት (ማለትም ለ10 ክፍለጊዜያት) ተምረዋል፡፡ እያንዳንዱ ክፍለጊዜም 40 ደቂቃዎች ነበሩት፡፡ በመጨረሻም ሁለቱም ቡድኖች አንድ አይነት የድህረትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ የጥናቱ ነድፍ በበሚከተለው ሰንጠረዥ 3.1 ላይ ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 3.1**፤ የጥናቱ ንድፍ

| የቡድን | ቅድመትምህርት ፈተና (pretest) | የሀሳብ ድር ብልሀት | ድህረትምህርት ፈተና (posttest) |
|---|---|---|---|
| የፍትነት | ✓ | ✓ | ✓ |
| የቁጥጥር | ✓ | X | ✓ |

ሰንጠረዥ 3.1 እንደሚያመለክተው ፍትነቱ ከመተግበሩ አስቀድሞ የፍትነት ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች አንድ አይነት የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ የፈተናው መረጃዎች ተተንትነው ከፍትነቱ ትግበራ አስቀድሞ ከቃላት እውቀት አኳያ በፍትነት ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች መካከል ጉልህ የስታትስቲክስ ልዩነት እንደሌለ ከታወቀ በኂላ ፍትነቱ ተተግብሯል፡፡ የፍትነቱ አተገባበር የተካሄደውም፣ ፍትነቱ

ቡድን ተሳታፊዎች በሃሳብ ድር ብልሃት፣ የቁጥጥሩ ቡድን ተሳታፊዎች ደግሞ በተማሪ መጽሃፉና በመምህር መምሪያው ላይ በተመለከተው መሰረት ቃላትን እንዲማሩ ተደርጎ ነው። በዚህ መንገድ ፍትነቱ የተተገበረውም እያንዳንዱ ቡድን ለ10 ክፍለጊዜያት እንዲማር በማድረግ ነው። የፍትነቱ ትግበራ እንደተጠናቀቀ የሁለቱ ቡድኖች ተሳታፊዎች አንድ ዓይነት የድህረትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና ተፈትነዋል፤ በመጨረሻም በፈተና የተገኙት መረጃዎች ተደራጅተው ተተንትነው በሁለቱ ቡድኖች መካከል የቃላት እውቀት ውጤት ልዩነት መከሰት አለመከሰቱ ተፈትሿል።

## 3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች

ይህ ጥናት የተካሄደው በሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተሳታፊነት ነው። የሰባተኛ ክፍል የተመረጠው የመጀመሪያ ደረጃ ቅድመ የትምህርት እርከን ማጠናቀቂያ በመሆኑ ነው። ስምንተኛ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከን ማጠናቀቂያ ቢሆንም ተማሪዎች ክልል አቀፍ ፈተና ተፈታኞች በመሆናቸው በጥናቱ ትግበራ ወቅት ትኩረት ላይሰጡ ይችላሉ በሚል ለጥናቱ አልተመረጠም። በስማዳ ወረዳ በወገዳ ከተማ ዙሪያ ካሉት አምስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአመች ናሙና (Convenince sampling) የወገዳ ሙሉ ሳይክል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለጥናቱ ተመርጧል። ትምህርት ቤቱ በዚህ የናሙና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም አጥኝዋ ከዚህ አካባቢ ስለምትሰራ ፍትነቱን ለማካሄድና ለምርምሩ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

የጥናቱ ተሳታፊዎችም በወገዳ ሙሉ ሳይክል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት በመማር ላይ ከነበሩት ስድስት የሰባተኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች መካከል በእጣ ናሙና በተመረጡ ሁለት ክፍሎች የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው። ክፍሎቹም 7ኛA እና 7ኛC ናቸው። በ7ኛA 45 ተማሪዎች ሲኖሩ፣ በ7ኛC ደግሞ 43 ተማሪዎች ነበሩ። እነዚህ ክፍሎች በእጣ ከተመረጡ በኋላም ተማሪዎቹ አንድ አይነት የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና በተመሳሳይ ጊዜ እንዲፈተኑ ተደርጓል። ከዚያም መረጃዎቹ ተተንትነው ሁለቱ የመማሪያ ክፍሎች በቃላት እውቀታቸው ተመጣጣኝ ሆነው በመገኘታቸው በተራ እጣ ናሙና አማካኝነት 7ኛA የቁጥጥር ቡድን፤ 7ኛC ደግሞ የፍትነት ቡድን ሆነው ተለይተዋል።

የፍትነቱ ቡድን በአማርኛ ቋንቋ የሃሳብ ድር ብልሃት ትምህርቱን የሚከታተሉ ተማሪዎች ሲሆኑ፣ የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ደግሞ ያለ ብልሃት (በሰባተኛ ክፍል በተማሪው መጽሀፍና በመምህሩ መምሪያ መስረት) የቃላት ትምህርት አቀራረብ እንዲማሩ ተድርጓል። በዚህ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ለመማር በሳምንት ሶስት ክፍለጊዚያት ተመድቦላቸዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት በትግበራው ወቅት የመደበኛውን የትምህርት ጊዜ ላለመሻማት እና በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ሳይሸፈኑ እንዳይቀሩ አንድ ክፈለጊዜ ብቻ ለጥናቱ ትምህርት መጠቀም የሚቻልበት ሁኔታ ስለሚሆን ነው። ይህም ጥናቱን ለማከናወን አመች ሁኔታ ስለሆነ በትግበራው ወቅትም የትምህርት ጊዜ በሳምንት ወደ ሶስት ክፍለጊዜ ለማሳደግ የተሻለ ስለሆነ ነው።

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃላት እውቀት ፈተና አማካይነት ነው። ፈተናው በአጥኚዋ ተዘጋጅቶ በቅድመትምህርት እና በድህረትምህርት ወቅት ከፍትነት ቡድኑና ከቁጥጥር ቡድኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች የቃላት እውቀትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሏል። ቅድመትምህርት ፈተናው ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች ከፍትነቱ አሰቀድሞ በቃላት እውቀት አኳያ ተመጣጣኝ ችሎታ ያላቸው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመለካት ነው። የድህረትምህርት ፈተናው አላማ ደግሞ ፍትነቱ እንደተጠናቀቀ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የቃላት ችሎታ ልዩነት ተከስቶ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መረጃ ለማግኘት ነው።

የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት ፈተናው አንድ አይነት እንዲሆን ተደርጎ ተዘጋጅቷል፤ አንድ አይነት እንዲሆን የተደረገበት መሰረታዊ ምክንያትም የቅድመትምህርቱና የድህረትምህርቱ ፈተናዎች መለያየት በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድር በመስጋት ነው። ፈተናው ሀያ ሶስት የምርጫ ጥያቄዎች (እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አማራጭ መልሶች) አካቶ የተዘጋጀ ነው። ሁሉም ጥያቄዎች ምርጫ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያትም በእርማት ወቅት ተጨባጭ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል ነው።

ፈተናው የሰባተኛ ክፍልን የተማሪ መጽሃፍና የመምህር መምሪያ መሰረት አድርጎ በአጥኚዋ ከተዘጋጀ በኋላ የቋንቋ አጠቃቀሙ፣ የቃላቱ ሁኔታ፣ የጥያቄዎቹ አጻጻፍ፣ ወዘተ.

የተማሪዎችን ችሎታ የሚመጥን ስለመሆኑ በሁለት የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲገመግምና አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል። ከዚያም የጥናቱ አማካሪ አንብበው አስተያየት ሰጥተውበታል።

የመምህራኑን እና የአማካሪውን አስተያየት በማካተት እንደገና በአጥኝዋ ከተሻሻለ በኋላም በዋናው ጥናት የማይሳተፉ 48 የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጎ የሙከራ ጥናት (pilot study) ተካሂዶበታል። ፈተናው በአጥኝዋ ከታረመ፣ ውጤቱም በውጤት ማስፈሪያ ላይ ከተመዘገበና ከተደራጀ በኋላ አስተማማኝነቱ በኩድር-ሪቻርድሰን 20 ($KR_{20}$) ተፈትሿል። አሰተማማኝነቱ በ$KR_{20}$ የተሰላበት ምክንያት ከየጥያቄዎቹ አኳያ እያንዳንዱ ተፈታኝ ያስመዘገበው ውጤት 0 ወይም 1 እንደመሆኑ ለትንተናው ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው። በዚህ መሰረት የፈተናው አስተማማኝነት $KR_{20}$ = .78 ሆኗል። ፈተናው አስተማማኝ ሆኖ በመገኘቱ ለዋናው ጥናት ከፍትነቱ ቡድንና ከቁጥጥሩ ቡድን የጥናቱ ተሳታፊዎች መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሏል። (ለሙከራ ጥናቱ የተሰበሰበው የቃላት እውቀት ፈተና መረጃ አባሪ መ ላይ ተመልክቷል)።

በቅድመትምህርቱ የቃላት እውቀት ፈተና አማካይ ውጤት የቃላት እውቀት ፈተና ውጤት ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ሲባል መረጃዎቹ በነጻ ናሙና ተ-ቴስት ተፈትሸዋል፤ ውጤቱም t(86) =-0.05, p =.96) ሆኗል። የድህረትምህርት የቃላት እወቀት መለኪያ ፈተና ተፈትነው፤በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ሲባል የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተካሂዷል። የተገኘው ውጤትም t(86) = 2.98, *P* = .004) በሁለቱ ቡድኖች መካከል የፍትነት ቡድኑ በልጦ ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል።

የፍትነት ቡድንና የቁጥጥር ቡድን የድህረትምህርት የቃላት እውቀት የአማካይ ውጤት ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ሲባል የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተካሂዷል። የተገኘው ውጤትም t(86) = 2.98, *P* = .004) በሁለቱ ቡድኖች መካከል የፍትነት ቡድኑ በልጦ ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል።

## 3.4. የማስተማሪያ ምንባቦችና መልመጃዎች ዝግጅት

የፍትነቱ ቡድንና የቁጥጥሩ ቡድን ተሳታፊዎች ቃላትን ለማስተማር በክፍል ደረጃው የተዘጋጀው የመማሪያ መጽሀፍ አግልግሎት ላይ ውሏል። Gu (2003) እና Nation (2001) እንደሚያስረዱት በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ከሚሳድሩ ተላውጦዎች አንዱ የማስተማሪያ መሳሪያው ተገቢነት እንዲሁም ክብደትና ቅለት ነው፤ ለዚህም ፍትነቱ በተማሪዎች ውጤት ላይ ያመጣውን ለውጥ ለማረጋገጥ ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን የተማሪ መጽሃፍና የመምህር መምሪያ መገልገል ተገቢ ነው። በዚህም መሰረት በሰባተኛ ክፍል የተማሪ መጽሃፍ ላይ የሚገኙት ምንባቦችና የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለፍትነቱ በስራ ላይ ውለዋል። ምክንያቱም የመማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለክፍል ደረጃው ተመጥኖ የተዘጋጀ በመሆኑ በጥናቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ተላውጦዎችን ለመቀነስ ስለሚረዳ ነው። ከቃላት ትምህርት መልመጃዎቹ ወይም ተግባራቱ አኳያ ግን ለቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች በተማሪ መጽሃፉ ላይ ያሉትን እንዳሉ ተተግብረዋል። ለፍትነት ቡድኑ ተሳታፊዎች ግን በተማሪ መጽሀፉ ላይ የሚገኙት መልመጃዎች ወይም ተግባራት በሃሳብ ድር ብልሃት አኳያ እንዲዘጋጁ ተደርጎ በስራ ላይ ውለዋል።

Gu (2003) እንደሚያስረዱት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና ውጤታማነት በሚቀርቡት ተግባራትና በመማሪያ አውዱ ምቹነት ላይ የተመሰረተ ነው፤ ማለትም የቃላት እውቀት ብልሀቶችን ማስተማር ውጤታማ የሚሆነው ብልሀቶቹን በአውድ ሊያለማምዱ የሚችሉ ተገቢ የቃላት ተግባራት ሲቀርቡ ነው። ይህን ሃሳብ መሰረት በማድረግ ለፍትነት ቡድኑ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች የእያናዳንዱን የሀሳብ ድር የቃላት አጠቃቀም በአውድ ማስተማርን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት እንዲማሩ ተደርጓል። (ማስተማሪያ መሳሪያ አባሪ ሐ ለተማሪዎች ለጥናቱ ተግባራ የተዘጋጀ የማስተማሪያ ማንዋል ተመልክቷል)።

በትምህርቱ ጊዜም ለሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበውን ሁለት ክፍለጊዜ ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም አስቸጋሪ ነበር። ምክንያቱም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉትንና የታቀዱትን ተግባራት ለመሸፈን የሚያስችል አልነበረም። ስለዚህ ከመደበኛው የትምህርት ስዓት አንድ ክፍለዘጊዜ በማመቻቸትና አንድ ክፍለጊዜ ከትምህርት ሰዓት ወጭ ፕሮግራም

በማስያዝ ሁለቱም ቡድን በተመሳሳይ ቦታና ጊዜ በሳምንት ሶስት ጊዜ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ (አንድ ክፍለጊዜ 40 ደቂቃ ነው)፡፡

## 3.5. የጥናቱ ሂደት

የጥናቱ መሰረታዊ አላማ የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቅት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ ለመፈተሽ ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ጥናቱ በሚከተለው መንገድ ተከናውኗል፡፡

በመጀመሪያ ጥናቱ የተካሄደበት ትምህርት ቤት በአመች ናሙና ተመርጧል፤ ከዚያም ጥናቱን ለማካሄድ ትምህርት ቤቱ ፈቃደኛ ስለመሆኑ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ እንዲሁም የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተጠይቀዋል፡፡ የትምህርት ቤቱ እና የተማሪዎቹ ፈቃደኝነት እንደተገኘም በሃሳብ ድር ብልሀት ቃላትን የማስተማር ቅደምተከተላዊ አተገባበር የሚመለከት ስልጠና ፍትነቱን ለሚተገበሩት የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህርት በአጥኝዋ አማካኝነት ቅዳሜና እሁድ 24/07/2014 ዓ.ም እስከ 25/07/2014 ዓ.ም ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ስልጠናውም አምስት ሰአትን ወስዷል፤ ቅዳሜና እሁድ የሆነበት ምክንያት መደበኛ ትምህርት ባለመኖሩ ብልሃቱ እንዴት እንደሚተገበር ለማሰልጠን ሰፊ ጊዜ ለማግኘት ሲባል ነው፡፡ ስልጠናው በመማሪያ ክፍል ውስት የተካሄደ ሲሆን፣ በመጀመሪያ ጽንሰሃሳቡን ለተግባሪ መምህሯ በማብራራት፣ ኪዚያም አርአያ ሆኖ ሰርቶ በማሳየት፣ በመቀጠል ከተማሪዎች ጋር እንዴት በጋራ መስራት እንደሚቻል፣ በመጨረሻም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ በማድረግ ሃላፊነት በሂደት የማሸጋገር ሞዴል መርህ ላይ ተመስርቶ የአሰልጣኝነት ስልጠና በመስጠት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፍትነቱ የመተግበር አቅም ተፈጥሮ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ (በሀሳብ ድር ብልሃት  ቃላትን የማስተማር ዘዴ የተሰጠ ስልጠና ማንዋል አባሪ ለ ተመልክቷል)፡፡

የቃላት እውቀትን ለመለካት ያገለገለው የቃላት እውቀት ፈተና ለዋናው ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከመዋላቸው አስቀድሞ በመከራ ጥናቱ (pilot study) ወቅት በዋናው ጥናት የማይሳተፉ በስማዳ ወረዳ በወገዳ ሙሉሳይክል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የሰባተኛ ክፍል 48 ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጎ አስተማማኝነቱ በኩድር-ሪቻርድሰን 20

($KR_{20}$) ተፈትሿል። ከዚያም ፈተናው ለዋናው ጥናት ከፍትነቱ ቡድንና ከቁጥጥሩ ቡድን የጥናቱ ተሳታፊዎች መረጃዎችን ለመሰብሰብ አገልግሏል።

ይህን ተከትሎም፣ በጥናቱ የሚካተቱት ሁለት የሰባተኛ ክፍሎች (ማለትም 7ኛA እና 7ኛC) በእጣ አማካይነት ተመርጠው ሁለቱም ክፍሎች አስተማማኝነቱና ተገቢነቱ በሙከራ ጥናት (pilot study) የተፈተሸውን ተመሳሳይ የቅድመትምህርት የቃላት ችሎታ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል። ፈተናው ታርሞ ውጤቱ ከተደራጀና ከተተነተነ በኋላ ሁለቱም ክፍሎች በቃላት ችሎታቸው ተመጣጣኝ እንደሆኑ በመታወቁ በእጣ ናሙና አማካይነት 7ኛA የቁጥጥር ቡድን፣ 7ኛC ደግሞ የፍትነት ቡድን ሆነው ተመድበዋል።

ሁለቱም ቡድኖች ከ03/08/2014 ዓ.ም እስከ 02/10/2014 ዓ.ም ድረስ ለስምንት ሳምንታት (ለአስር ክፍለጊዜያት) ቃላትን ተምረዋል። የፍትነቱ ቡድን ተሳታፊዎችም በሃሳብ ድር ብልሃት አማካይነት፣ የቁጥጥሩ ቡድን ተሳታፊዎችም ደግሞ በተማሪ መጽሃፍና በመምህር መምሪያ መሰረት ቃላትን ለተመሳሳይ የክፍለጊዜ ብዛት እንዲማሩ ተደርጓል። የፍትነቱ ቡድን ተሳታፊዎች በሃሳብ ድር ብልሃት ከመማራቸው ውጪ የሁለቱም ቡድኖች ተሳታፊዎች በተመሳሳይ መምህርት መተማሪው መጽሀፍ በሚገኙት ተመሳሳይ የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ተከታትለዋል ማለት ነው።

የፍትነቱ ትግበራ እንደተጠናቀቀ የሁሉቱ ቡድን የጥናቱ ተሳታፊዎች ፈተና የድህረትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና እንዲፈተኑ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የድህረትምህርት የቃላት ፈተናው በአጥኝዋ ከታረመ በኋላ የሁለቱ ቡድኖች ውጤቶች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት አማካይነት ተተንትነዋል።

## 3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት የፍትነት ትግበራው ከመጀመሩ በፊት በቅድመትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና፣ እንዲሁም ትግበራው ከተጠናቀቀ በኋላ በድህረትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና ከቁጥጥር ቡድኑ እና ከፍትነት ቡድኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል (የቅድመትምህርት ፈተናው እና የድህረትምህርት ፈተናው መረጃዎች በአባሪ ሀ ላይ ተመልክቷል)። ከዚያም በቅድመትም ህርትየቃላት እውቀት አኳያ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የስታትስቲክስ ልዩነ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለመፈተሽ ሲባል መረጃዎቹ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል።

እንዲሁም በድህረትምህርት በቃላት እውቀት አንጻር በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የስታትስቲክስ ልዩነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለመፈተሽ ሲባል በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል። ከትንተናው አስቀድሞ በቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የቃላት ፈተና የተገኙት መረጃዎች የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረታዊ እሙን (assumption) የሆነውን ወጥ ስርጭት (normal distribution) የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሲባል የኮልጎሞሮብ-ሲሚኒሮብ ፍተሻ ተካሂዷል፤ በዚህም መሰረት በቅድመትምህርት ፈተናው አኳያ የፍትነት ቡድን P = .087፤ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ P = .070 በመሆኑ እሙኑ መሟላቱን ለማወቅ ተችሏል። በድህረትምህርት ፈተናው አንጻርም የፍትነት ቡድኑ መረጃ ውጤት P = .200 በመሆኑ እሙኑ መሟላቱ ታውቋል። ቁጥጥር ቡድኑ መረጃ ውጤት ግን P = .002 በመሆኑ የእሙኑን መሟላት አጠራጣሪ አድርጎታል።

በመሆኑም ይህን የድህረትምህርት የቁጥጥር ቡድኑ መረጃ የስርጭት ወጥነት በግድለት (Skewness) በመደበኛው ውጤት እና በዝብጠት (Kurtosis) መደበኛ ውጤት መፈተሽ አስፈላጊ ሆኗል። በፍተሻውም የግድለት መደበኛ ውጤቱ -1.41 ሲሆን የዝብጠት መደበኛ ውጤቱ ደግሞ 1.00 ሆኗል። ከውጤቶቹም መረጃዎቹ የስርጭት ወጥነት እንደሚያሟሉ ለመረዳት ተችሏል (በኮልሞጎሮብ-ሲሚኒሮብ እና የዜድ ውጤት ስሌቶቹ በአባሪ ሰ ላይ ተመልክተዋል)። እሙኑ በዚህ መንገድ ተፈትሾ መሟላቱ ከተረጋገጠ በኋላ መረጃዎቹ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል። ነጻ ተላውጦው በጥገኛ ተላውጦው ላይ ያሳደረው የተጽእኖ መጠንም (effect size) በኮህን ዲ (Cohen’s d) ተሰልቷል።

# ምዕራፍ አራት፤ የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

## 4.1. የውጤት ትንተና

ይህ ጥናት የተካሄደው "የሃሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ምን ነውያህል ነው?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲባል ነበር።

ጥያቄዎችን ለመመለስም ሲባል በቃላት ፈተና ከጥናቱ የፍትነት ቡድንና የቁጥጥር ቡድን የጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰቡ የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት መረጃዎች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል።

በዚህም መሰረት ፍትነቱ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ሁለቱ ቡድኖች የጥናቱ ታሳታፊዎች በቃላት እውቀታቸው አኳያ ያላቸውን ተመጣጣኝነት ለመለካት ሲባል አንድ አይነት የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነው ውጤታቸው ለትንተና ተመዝቧል (የፍትነቱ ቡድን እና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርት ውጤት በአባሪ ሠ ላይ ተመልክቷል)። መረጃዎቹም በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሸዋል። የትንተናው ውጤትም በሰንጠረዥ 4.1 ላይ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 4.1፤ የቡድኖቹ የቅድመትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና ውጤት ፍተሻ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ተላውጦ | ቡድን | ናሙና (n) | አማካይ ውጤት | መደበኛልይይት | የቲዋጋ (t) | የነጻነትደረጃ (df) | ጉልህነት (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላትእውቀት | የፍትነት | 43 | 14.77 | 3.52 | -0.05 | 86 | .96 |
| | የቁጥጥር | 45 | 14.80 | 2.94 | | | |

በሰንጠረዥ 4.1፤ እንደተመለከተው በቅድመትምህርቱ የቃላት እውቀት ፈተና አማካይ ውጤት የፍትነት ቡድኑ ከቀጥጥር ቡድኑ በ0.03 ከፍ ይላል። በመደበኛ ልይይትም እንዲሁ የፍትነት ቡድኑ በ0.58 ይበልጣል። ይህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የቃላት እውቀት

ፈተና ውጤት ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ሲባል መረጃዎቹ በነጻ ናሙና ተ-ቴስት ተፈትሸዋል፤ ውጤቱም t(86) = -0.05, p =.96) ሆኗል። ይህ በፍትነት ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ የቃላት ፈተና ውጤቶች መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት የሌለ መሆኑን ያሳያል። ከዚህም ከፍትነቱ በፊት ሁለቱ የጥናቱ ተሰታፊ ቡድኖች በቃላት እውቀታቸው ተመጣጣኝ እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል።

የፍትነቱ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች ከፍትነቱ በፊት ተመጣጣኝ የቃላት እውቀት እንደነበራቸው በሰንጠረዥ 4.1 ላይ በተመለከተው መሰረት ተረጋግጦ ፍትነቱ ከተተገበረ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች አንድ አይነት የድህረትምህርት የቃላት እወቀት መለኪያ ፈተና ተፈትነዋል። ከዚያም በአማካኝ ውጤቶቻቸው መካከል ያለው ልዩነት በነጻ ናሙና ቲ- ቴስት ተፈትሿል፤ የቲ- ቴስት ውጤቱም 4.2 ተመልክቷል። (የፍትነት ቡድን እና የቁጥጥር ቡድን የድህረትምህርት ፈተና ውጤቶች በአባሪ ረ ላይ ይመለከቷል)።

ሰንጠረዥ 4.2 የፍትነት ቡድንና የቁጥጥር ቡድን የድህረትምህርት የቃላት እውቀት ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ተላውጦ | ቡድን | ናሙና (n) | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲዋጋ (t) | የነጻነትደረጃ (df) | ጉልህነት (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላትእውቀት | የፍትነት | 43 | 16.84 | 2.44 | 2.98 | 86 | .004 |
| | የቁጥጥር | 45 | 15.36 | 2.22 | | | |

ሰንጠረዥ 4.2 እንደሚያመለክተው በአማካይ ውጤት አኳያ የፍትነት ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በ1.48 ይበልጣል። በመደበኛ ልይይትም እንዲሁ የፍትነት ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በ0.22 ይበልጣል። በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ ሲባል የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተካሂዷል። የተገኘው ውጤትም t(86) = 2.98, *P* = .004) በሁለቱ ቡድኖች መካከል የፍትነት ቡድኑ በልጦ ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። ከዚህም፣ የፍትነት ቡድኑ ተሳታፊዎች በሃሳብ ድር ብልሃት፣ የቁጥጥር ቡድኑ ተሳታፊዎች ደግሞ በመምህር መምሪያና በተማሪ መጽሃፉ

አማካይነት ቃላትን ተምረው ፍትነቱ እንደተጠናቀቀ፤ የፍትነት ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ በልጦ በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ማሳየቱን ያመለክታል፡፡ ለዚህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ለታየው የቃላት እወቀት ውጤት ልዩነትም የፍትነቱ ቡድን ቃላትን በሃሳብ ድር ብልሃት አማካይነት ማስተማሩ አስተዋጽኦ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡

የሃሳብ ድር ብልሃት ትግበራ በተማሪዎች የቃላት እውቀት ላይ ያሳደረው የተጽእኖ ድረጃም (Effect Size) በኮሀን ዲ (Cohen's d) ቀመር ተሰልቷል፡፡ የተገኘው ውጤትም የተፅኖ መጠን = 0.63 ሆኗል፡፡ ከዚህም ነጻ ተላውጦው በጥገኛ ተላውጦው ላይ ያለው የተጽእኖ መጠን መካከለኛ እንደሆነ ለማዎቅ ተችሏል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መፈተሽ ነበር፡፡ ጥያቄውን ለመፈተሽም መረጀዎቹ በቃላት ፈተና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ተሰብስበው በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱ መስታዊ ጥያቄ "የሃሳብ ድር ብልሃት የተማሪዎችን የቃላት እወቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?" የሚለውን ጥያቄ ለመፈተሽም መረጃው በነፃ ናሙና ቲቴስት ተተንተኗል፡፡ የሃሳብ ድር ብልሃት ቃላትን የተማሩት የፍትነቱ ቡድን ተሳታፊዎች የድህረትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም በሃሳብ ድር ብልሃት የተማሩ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ የስታትስቲክስ ብልጫ አሳይቷል፡፡ (ሰንጠረዥ 4.2ን ይመለከቷል)፡፡

በመሆኑም የሀሳብ ድር ብልሃት ተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማጎልበት አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ውጤትም የሀሳብ ድር ብልሃት የቃላት እውቀትን ለማሳደግ የሚረዳ ብልሃት መሆኑን አሳይቷል፡፡ ከዚህ ጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የሀሳበ ድር ብልሃት የቃላት እውቀት ችግር ላለባቸውን ተማሪዎች ከፍተኛ አስተዋጸኦ ያለው መሆኑን ነው ቢባልም ተጠይቃዊ ይሆናል፡፡

Anders፣ Bos፣ Allen፣ እና Fillip (1984) እና Bos፣ Anders፣ Fillp እና Jaffe (1989) በሁለት የማስተማር ዘዴዎች ተፅዕኖ ዙሪያ ጥናት ያደረጉት ሲሆን እነዚህም የስነ-ፍች ጥናት የሁኔታ ትንተና በተቃርኖ በመዝገበቃላት ቃላትን የማስተማር ብልሃት ላይ ሆኖ

ጥናቱ  የተደረገውም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመማር እንከን ያለባቸው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የነዚህን የሁለቱን የቃላት የማስተማር ሂደት ከተተናቀቀ በኂላ ለሁለቱም ቡድኖች ቃላትን መሰረት ያደረገ አንበቦ የመረዳት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ውጤቱም ያሳየው በስነፍች ጥናት የሁኔታ ትንተና ብልሀት ቃላትን የተማሩ ተማሪዎች በመዝገበቃላት ቃላትን ከማስተማር ብልሀት በላቀ ውጤታማ መሆናቸውን የሚየሳይ ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር በቃላት ማስተማር ብልሀት የተጠና በመሆኑ ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤ በሁለተኛ ደረጀ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመማር እንከን ያለባቸው ተማሪዎች ላይ የተጠና በመሆኑና  የመረጃ መሰብሰቢያው ቃላትን መሰረት ያደረገ አንብቦ የመረዳት ፈተና የተሰጠ በመሆኑ  ልዩነት አለው፡፡

Fore፣ Boon፣ Lowrie (2007) ላይ የሀሳብ ድር የማስተማር ብልሀት በመዝገበቃላት በስድስት የመማር ችግር ባለባቸው መለስተኛ ተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕእኖ አጥንተዋል፡፡ በማስተማር ብልሀቱ፣ ቃላት የቃላት አውቀት ላይ ማስተማራቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤ በመዝገበቃላት የማስተማር ዘዴ በስድስት የመማር ችግር ባለባቸው መለስተኛ ተማሪዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖ ያጠኑ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ከተሳታፊዎች አንጻርም ልዩነት አለው፡፡

Hairrell (2011)፣ Rupley እና Nichols (2005) በሀሳብ ድር ብልሀት የማስተማር ብልሃት የሚጠቀሙ ሲሆን አገልግሎቱም አዳዲስ ቃላትን ትርጉም በመፈለግ፣ ትርጉም በመስጠት በቃላቱ አማካይነት አረፍተነገር በመስራት ላይ ያተኩራል፡፡ የእያንዳንዱ የማስተማር ብልሀት ካጠናቀቁ በኂላ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማወቅ መመዘኛ የቀረበላቸው ሲሆን አላማውም የአዳዲስ ቃላት እውቀታቸውን ለመገምገም ነው፡፡ ውጤቱም የሚያሳየው አዳዲስ ቃላትን በመዝገበቃላት ከማስተማር ብልሀት ይልቅ በሀሳብ ድር ብልሀት በመጠቀም ቃላትን ማስተማር በሁሉም ስድስት ተማሪዎች የበለጠ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር

በሃሳብ ድር ብልሀት ቃላትን ማስተማራቸው እና ውጤቱም ቃላትን በመዝገበቃላት ከማስተማር ብልሀት ይልቅ በሃሳብ ድር ብልሀት በመጠቀም  ማስተማር  የበለጠ እንደሆነ ማሳየቱ ተደጋጋፊነት አለው፤ የመረጃ መሰብሰቢያው ግን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማወቅ መመዘኛ የቀረበላቸው በመሆኑና በስድስት ተማሪዎች ላይ መረጃው የተሰበሰበ በመሆኑ ጋር ይለያል፡፡

Nunan (1991) እንደሚያብራሩት፣ ቃላትን ማስተማር ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገውን ቃላትን ለማስተማር የሚያስችሉ ሁኔዎችን ማመቻቸትም ጭምር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ምክኒያቱም ተማሪዎች የቃላት መማር ዘዴዎችን የሚተዋወቁበት እድሎች ከተመቻቹላቸው በአግባቡ ሊማሩና የቃላት እውቀታቸው ሊያዳብሩ ይችላሉ፤ የዚህ ጥናት ውጤትም ከዚህ ሃሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የዚህ ጥናት ውጤት የቃላት ትምህርት ብልሃቶችን ለቋንቋ ተማሪዎች ክፍል ውስጥም ሆነ ክፍል ውጭ አዳዲስ ቃላትን በራሳቸው መንገድ በቀላሉ እንዲማሩ ይረዳቸዋል፤ የሚለውን የSchmitt (1997) እና የOxford (2003) ሀሳብ የሚያጠናክር ሆኗል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የዚህ ጥናት ውጤት በቋንቋ ትምህርት የቃላት መማሪያ ብልሃቶች ተማሪዎች ቃላትን በራሳቸው እንዲማሩ፣ ለቃላት አጠቃቀም አፅንኦት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፤ በዚህም የቃላት እውቀታቸውን ለማጎልበት ያስችሏቸዋል፤ የሚለው የመስኩ ምሁራን (Tudor፣ 1996፤ Oxford፣ 1990)፡፡ ) ሃሳብ ያጠናክራል፡፡

እንዲሁም የዚህ ጥናት ውጤት ብልሃቶችን መጠቀምን ከበቂ ልምድ ጋር ቃላትን የተማሩ ተማሪዎች ብልሃቶችን በመጠቀም ልምዱ ከሌላቸው ተማሪዎች የበለጠ ይማራሉ፤ ሲሉ Omalley እና Chamot (1990) ከሚያቀርቡት ሃሳበ ጋር የሚስማማ ነው፡፡

በመሆኑም ከዚህ የጥናት ግኝት በመነሳት የሃሳብ ድር ብልሃት ቃላትን በማስተማር ተማሪዎችን በራስ የመተማመን ሁኔታና ንቁ ተሳታፊ በማድረግ የቃላትን ተመሳሳይ ፍች፣ ተቃራኒ ፍች፣ መዝገበዋላዊ ፍችና አውዳዊ ፍች ለመመርመርና ትርጉም ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ ስነትምህርታዊ ትርጓሜ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ምክኒያቱም ብልሃቱ የቃላት እውቀት ችግር ላለባቸው በአግባቡ ከተተገበረ ይህን ችግራቸውን ለመፍታት በመምህሩ መምሪያና በተማሪው መጽሃፍ ከሚሰጠው (ከተለመደው ቃላት የማስተማር ዘዴ) በበለጠ ሁኔታ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ለማየት ተችሏል፡፡

የBrown & Perry (1991) ጥናትም በሁለት ቡድን ቅድመትህርትና ድህረትምህርት ውጤት ላይ ተመስርቶ የተሰራ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎችን ሁለት የትውስታ ብልሃቶችን ብቻ በማስተማር የተገኘ ውጤት በመሆኑና መቅድመትምህርተና በድህረትምህርት ከመሆኑም ባሻገር በቅድመትምርትና በድህረትምህርት የተማሪዎች የብልሀት አጠቃቀማቸው ባልተለካበት ሁኔታ በፈተና ብቻ

የተገኘ ውጤት በመሆኑና ሁለቱ ቡድኖች በተለያየ መምህር ተምረው የተገኘ ውጤት መሆኑ ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር የአጠናናን ልዩነት እንዳለው ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና አላማ የሃሳብ ድር ብልሃት  የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ ለመመርመር የተካሄደ ነበር፤

በጥናቱ መልስ ያገኘው የመርምሩ መሪስታዊ ጥያቄ የሃሳብ ድር ብልሃት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?

ጥናቱ ላነሳው ጥያቄ  ተገቢ ምላሽ ለመስጠት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በዚህ መሰረትም ጥናቱን ለማከናወን በደ/ጎንደር ዞን ስማዳ ወረዳ ወገዳ ከተማ ከሚገኙት አምስት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች መካከል የወገዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡ የተመረጠውም የወገዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ከሚገኙት ስድስት የሰባተኛ የመማሪያ ክፍሎች የሁለት ክፍል ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ ከተለዩ በኋላ የፍተነት ቡድንና  የቁጥጥር ቡድን በእጣ ተለይተው ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢነትም የቃላት እውቀት ፈተና ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የቃላት እውቀት ፈተናዎቹም በቋንቋ መምህራንና በጥናቱ አማካሪ ተገቢነታቸው ተፈትሿል፡፡ የመመህራኑና የአማካሪውን አስተየየት በማካተት ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ ከአስተማማኝነታቸው አንጻርም የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ በኩድር-ሪቻረድሰን 20 (KR20) ተለክተው እስተማማኝ መሆናቸው ተረጋግጦ ተግባር ላይ ውሏል፡፡

በመቀጠል የሁለቱም ክፍሎች ተማሪዎች ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና ተፈትነው የተገኘው አማካይ ውጤቶች በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል የቃላት እውቀት ጉልህ ልዩነት ባለመገኛቱ የፍትነት ቡድንና የቁጥጥር ቡድኖች ተብለው በእጣ ተመድበዋል፡፡ የፍትነቱ ቡድን ተማሪዎች በሀሳብ ድር ብልሃት፣ የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች በመምህሩ መምሪያና በተማሪ መጽሀፍ መሰረት ለስምንት ሳምንታት (ለ10 ክፍለጊዚያት) ቃላት ተምረዋል፡፡ በመጨረሻም ሁለቱመ ቡድኖች ድህረትምህርት የቃላት እውቀት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ የተሰበሰቡት  መረጃዎች በነፃናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡

ከውጤት ትንተናው መረዳት እንደተቻለውም በሃሳብ ድር ብልሃት የተማሩት የፍትነቱ ቡድን ተማሪዎች የቃላት እወቀት ፈተና አማካይ ውጤት በመምህር መምሪያውና በተማሪው መፅሀፍ መሰረት ከተማሩት የኩጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የቃላት እውቀት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይቷል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሃሳብ ድር የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ መመርመር ነበር፤ ከዚህም በመነሳት የጥናቱን የትንተና ውጤት ማብራሪና ማጠቃለያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

1. የፍትነቱ ቡድን በሃሳብ ድር ብልሃት ከተማሩ በኋላ የቃላት እውቀት ፈተና አማካይ ውጤት በመምህሩ መምሪያና በተማሪው መጽሃፍ መሰረት የቃላት አቀራረብ ከተማሩት ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የቃላት እውቀት አማካይ ውጤት ተሽለው ተገኝተዋል፡፡
2. የሃሳብ ደር ብልሃት ቃላትን ማስተማር ከቃላት እውቀት ጋር ጥብቅ አዎንተዊ ግንኙነት ያለው መሆኑን ስለሚያሳይ ብልሃቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ቃላትን ለማስተማር ተግባር ላይ ቢውልና በስፋት ቢሰጥ መልካም ነው የሚል ጥቆማን ለመስጠት ያስደፍራል፡፡

## 5.3. አስተያየት

የጥናቱን ውጤትና መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ የሚከተሉት ስነትምህርታዊ መፍትሄዎች፣ ተጨማሪ የምርምር ጥቆማዎችና አሰተያቶች ተሰጥተዋል፡፡

1. የዚህ ጥናት ውጤት እንዳረጋገጠው የፍትነቱ ቡድን ተማሪዎች በየሃሳብ ድር ብልሃት ቃላትን ከተማሩ በኋላ የቃላት እውቀት አማካይ ውጤታቸው በመምህር መምሪያና በተማሪው መጽሃፍ መሰረት የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የቃላት እውቀት አማካይ ውጤት በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፤ በመሆኑም የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማጎልበት ብልሃቱን በተመለከተ በየድረጃው ለሚያስተምሩ ለቋንቋ መምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ስልጠና

መስጠትና የቃላት ተግባራትንም ለዚህ ብልሃት በሚያመች መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

2. የቃላት ትምህርት ግቡን ይመታ ዘንድ የተማሪዎች የሃሳብ ድር ዘዴ አተገባበር መጎልበት ይኖርበታል፤ ከዚህ ጥናት ውጤት መረዳት እንደተቻለው የፍትነቱ ቡድን ተማሪዎች በሃሳብ ድር ዘዴ ቃላትን መማራቸው የቃላት እወቅተ ፈተና ውጤት በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፤ በመሆኑም ብልሃቱ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ታውቋል፤ስለሆነም በአንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ለተማሪዎች በሃሳብ ድር ብልሃት ቃላትን ማስተማር እንዴት እንደሚተገበር ስልጠና በመስጠት ብልሃቱን በአግባቡ እንዲገለገሉበት ቢደረግ ጠቃሚ ነው፡፡

3. የአማርኛ ቋንቋ መማሪያን ማስተማሪያ መጽሃፍት አዘጋጆችም የቃላት እውቀትን ለማስተማር የሚያስችል አቀራረብ ተከትለው ቢያዘጋጁ ይመረጣል፡፡

ይህ ጥናት ያላተኮረባቸው እና በሰፊው ያልዳሰሳቸውን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የወደፊት የጥናት ጥቆማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. በዚህ ጥናት ውጤት መሰረት የሃሳብ ድር ብልሃት በመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የቃላት እውቀት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ያስችላል፤ የፍትነቱ ቡድን ተማሪዎች በሃሳብ ድር ብልሃት ቃላትን ከተማሩ በኋላ የቃላት እውቀት አማካይ ውጤት በመምህሩ መምሪያና በተማሪ መጽሃፍ መሰረት የቃላት ማስተማሪያ ብልሃት ከተማሩት ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸው በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ታይቷል፤ በመሆኑም በቀጣይ ጥናቶች ትኩረት ሰጥቶ በጥልቀት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

2. የሃሳብ ድር ብልሃት ተማሪዎች ያላቸውን የቃላት እውቀት በተናጥል አልፈተሸም፡፡ በመሆኑም በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች የሃሳብ ድር ብልሃት ተማሪዎችን በተናጥል የቃላት እውቀት በተመለከተ ጠለቅና ሰፋ ያለ ጥናት አካሂዶ መፈተሸ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ብልሃቱ በብዙ ናሙናዎች ላይና በሰፊ የጊዜ ገደብ በመተግበር በብልሃቱ የቃላት እውቀትን ለማጎልበት ያለውን ሚና በተመለከተ ቀጣይ ጥናት ማከናወን አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

3. ጥናቱ ከሌሎች የቃላት ማስተማሪያ ብልሃቶች ጋር በቅንጅት የቃላት እውቀት ላይ ያላቸውን አሰተዋጽኦ አልፈተሸም። በመሆኑም በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች የሃሳብ ድር ብልሃት ከሌሎች የቃላት ማስተማር ብልሃቶች ጋር በቅንጅት በቃላት እውቀት ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ በተመለከተ ጥልቅ ጥናት አካሂዶ ውጤታቸውን መፈተሽ ያስፈልጋል።

## ዋቢዎች

ሲሳይ ተበጀ። (1990)። "በአዲስ አበባ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስራ ላይ የዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ ቃላትን በማስተማር ረገድ ያለው ብቃት።" የማስተርስ ድግሪና ማሟያ ፁህፍ *አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*፣ አዲስ አበባ።

በላይነሽ ደነቀ። *(2002)። በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቃላትን የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች ፍተሻ። ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት አዲስ አበባ።*

በላይነሽ ደነቀ። (2010)። *"የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፤ጾታ ተኮር ሙከራዊ ጥናት (በዘነናኛ ክፍል ኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች) ተተኳሪነት"። (የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።*

ባየ ይማም። (1987)። *የአማርኛ ሰዋሰው።* አዲስ አበባ፣ ት.መ. ማ. ማ. ድ አሳታሚ።

*ብሩክታይት ተሰፋይ።(2001)። በመቀሌ ከተማ በሚገኙ ስስት ከፍተኛ ሁለትኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት የዘጠንኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ። ያልታተመ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት፣ አድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ትምህርት ቤት አድስ አበባ።*

ብርሃኑ ገበየሁ። (1997)። *የአማርኛ ስነ ግጥም።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አሳታሚዎች።

ትንሳኤ ብርሃኔ። (1988)። "የአማርኛ ቀላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት።" የሁለተኛ ድግሪ ማሙያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ትምህርት ሚኒስተርና አብክመ ትምህርት ቢሮ። (2007 ዓ.ም)። *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ፡ የተማሪ መጽሃፍ፣ 7ኛ ክፍል። አዲስ አበባ።*

ንጋቱ አሰፋ። (2000)። በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀምባቸው የቃላትን የመማር ብልሃት ምርምራ። ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት አዲስ አበባ።

አለሚቱ ጌታመሳይ።(2013)። "የቃላት ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት፣አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤ በኦሮሚያ ክልል በተዘጋጁ የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍት ተተኳሪነት" በሚል ለሁለተኛ ድግሪ መሟያ ቀረበ።

እሸቱ አጋ፡፡ (1997)፡፡ በአዲስአበባ በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁተለኛ ደረጃ ትምህርትላይያተኮረ ቃላት ትምህርት ውሰጥ አቀረራብ ግምገማ፡፡ *ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ መሚያ* ጥናት፣ አዲስአበባ ዩኒበርስቲ፣ድህረምረቃ ትምህርት፣አዲስ አበባ፡፡

የሻው ተሰማ፡፡ (1996)፡፡ *ልሳነ ብዕር ከመልሳነሰብ* ፡፡ አድስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት፡፡

ደረበ ሙሉ፡፡ (1999)፡፡ "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ዘጠነኛ ክፍል ቋንቋ *መተማሪዎች* የአማርኛ ምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ፡፡" *ያልተታመ* የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ድህረ ምረቃ ትምህት ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

ዳኛቸው ወርቁ፡፡ (1977)፡፡ *የፅሁፍ ጥበብ መመሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ኲራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

Alderson, J. C., Clapham, C. & Wall, D. (1995). Language Test Construction and Evaluation. Cambridge: Cambridge University Press.

Alderson, J.C. (2005). Diagnosing Foreign Language Proficiency: The interface between Learning and Assessment. New York: The Tower Building.

Al-Jarf, R. (2011). Teaching Spelling Skills with a mind-mapping software. Asian EFL ournal,.Oxford: Oxford Univrsity Press.

Allen, V.F. (1983). Techniques in Teachining Vocabulary. Oxford: Oxford Univrsity Press.

Alseweed, M.A. (2000). The Effects of Proficiency and Training on the Word-Solving.

Anders, P. L., Bos, C. S., & Filip, D. (1984). The effect of semantic feature analysis on the reading comprehension of learning-disabled students. In J. S. Niles & A.

B Brown, C. & Perry, F.L. (1991). Acomparison of Three Learning Strategies for ESLVocabulary Learning. *Research and Teaching ELT Journal, Vol. 25, No.2,oyle,J .P.(1987). Sex Differences in Listening Vocabulary. Language Learning.*

Baker, S. K., Simmons, D. C., & Kame'enui, E. J. (1998). *Vocabulary acquisition*: Research bases.

Biemiller, A. (2003). *Vocabulary: Needed if more children are to read well*. Reading Psychology.

Bornay, N. (2011). Explicit Strategy Training in Vocabulary Learning for beginning

Bornay, N. (2011). Explicit Strategy Training in Vocabulary Learning for beginning Spanish Students. *International Review of Social Sciences and Humanities.*

Bos ,C .S . , Allen , A . A . & Scanlon ,D. J.(1989). Vocabulary instruction and reading comprehension with milingual learning disabled students. National Reading Conference Yearbook. .

Bos, C. S., & Anders, P. L. (1990). Effects of interactive vocabulary instruction on the vocabulary learning and reading comprehension of junior-high learning disabled students. Learning Disability Quarterly.

Bos, C. S., Anders, P. L., Filip, D.,& Jaffe, L. E. (1989). The effects of an interactive instructional strategy for enhancing reading comprehension and conten are learning for students with learning disabilities. *Journal of Learning Disabilities.*

Bos, C. S.,& Anders,P.L.(1992). Using interactive teaching and learning strategies to promote text comprehension and content learning for students with learning disabilities. *International Journal of Disability, Development and Education.*

Brown, D.(2001). *Teaching by principles: An interactive approach to language pedagogy.* New York: Longman Pearson Education Company.

Brown, H. (1994). *Teachin by Priniciples*. London; Perntice Hall.

Budd, J. W. (2003). *Mind maps as classroom exercises.* Minnesota: University of Minnesota.

Budd, J.W. (2004). Mind maps as classroom exercise. *Journal of Economic Education, 35(1),Cambridge: Cambridge University Press.Children.*

Byrns,G. (2010). *A Comparison of multiple-strategy methods: Effects on fourth-grade students'general and content-specific reading comprehension and vocabularydevelopment.* Cambridge University Press. Cambridge: Cambridge University Press.

Carter, R. & McCarthy, M. (1998). Vocabuly and Language Teaching. London: Longman.Cunningham, A. E., & Stanovich, K. E. (1998). What reading does for the mind.

Chamot, A .U. (2005). *Language Learning Strategy Instruction: Current Issues and Trends. Annual Review of Applied Lingustics*, Vol.25, N0.2, pp.112-125

Coady, J. 1997). L2 Vocabulary A quisition: A Synthesis of Research. In J.Coady an Th.Hukin (Eds.), *Second Language Vcabulary Aquisition: A Rational for Pedagogy Cambridge:* Cambridge University Press.

Cohen, A. (1990). *Language Learning: Insights for Learners, Teachers, and Researchers.* Boston: Newbury House, Heinle & Heinl.

Doughty, C, J. (2009), *The Handbook of language teaching*. London: Wile Black well.

Ebbers, S. M., & Denton, C. A. (2008). A root awakening: Vocabulary instruction for older students with reading difficulties.

Etp. (1994)."Education and Training Policy."Addiss Abeba for secondary students: Challenges for struggling students and teachers.

Fore, C., Boon, R., & Lowrie, K. (2007). Vocabulary instruction for middle school students with learning disabilities: A comparison of two instructional models. Learning Disabilities: *A Contemporary Journal.*

Gairns, R. & S.Redman. (1986). *Working with Words: A Guide to Teaching and Learning Vocabulary.* Cambridge: CUP.

Gu, Y. & Johnson, R.K. (1996). *Vocabulary Learning Strategies and Language Learning out comes.* Uk: University of Hong kong.

Gu, Y. (2003).Vocabulary Learning in a Second Language: Person, Task, Context and Strategies. Teaching English as a Second Language.TESOL Quarterly, 7(2).

Hairrell, A., Simmons, D., Rupley, W., & Vaughn, S. (2011). An investigation of fourth grade teachers' use of vocabulary instruction in social studies. *Journal of Reading Education.*

Hant, A. & Belgar, D.(2002)."Crrent Researchand Practice inTeaching Vocabulary. Rechards, J. and Willy Renandya (eds.) ,*Methodology in Language Teaching; AnAnthology of Crrunt Practice.* Cambridge; Cambridge Colour Press.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching*. New York: Longman Group UK Limited.

Hatch, E. & Brown, C. (1995). Vocabulary, Semantic & Language Education.

Hirsch, E. D., Jr. (2003). Reading comprehension requires knowledge of words and the world: Scientific insights into the fourth-grade slump and the nation's stagnant comprehension scores.

Hofland, C. (2007).Mind mapping in the EFL class room. Retrieved from http://hbokennisbank.uvt.nl/cgi/fontys/show.cgi?fid=4166. instructional strategy for enhancing reading comprehension and content area

Jitendra, A., Edwards, L., Sacks, G., & Jacobson, L. (2004). What research says about Learning Disabilities: *A Contemporary Journal,Learning Disability Quarterly, learning for students with learning disabilities. Journal of Learning Disabilities, Journal of Research on Educational Effectiveness.*

Little ,D.(1994).Words and Their Properties :Argumments for a Lexcal Approach to Pedagogical Grammer Universty Press .

Liu,Y.,Zhao, G., & Bo,Y. (2014). The effect of mind mapping on teaching and learning: a meta-analysis.Standard Journal of Education and Essay.

Macaro, E.(2001).Learnining Strategies in Foreign and Secon Languge Class room. London: Continuum.

Mastropieri, M.,Scruggs, T., & Graetz, J. (2003). Reading comprehension instruction

McCarthy, M. (1990). *Vocabulary.* Oxford: Oxford University Presss.

McCrostie, J. (2007). Examming Learner Vocabulary Note Books. *ELT Journal,*

Miao, X.(2007).Combined research on the teaching of vocabulary in middle school metacognitive strategies and mind map.Unpublished Doctoral Dissertation, University of Alabama.

Mitchell, R., Myles, F., & Marsden, E. (2013). *Second Language Learning Theories*. Routledge.

Nagy, W. E., & Anderson, R. C. (1984). How many words are there in printed school English? Reading Research Quarterly.

Nagy, W. E., Herman, P. A., & Anderson, R. C. (1985). Learning words from context.

Nasar.R.t.(1979 4th ed). Teaching and Learning English. London; Zowe and Brydon Printers Ltd.

Nation, I.S. P. (2001).Learning vocabulary in another language. Cambridge:

Nation, P. (2000).Learning Vocabulary in Lexical Sets: Dangers and Guidelines.

Nation, P. (2001). Learning Vocabulary in Another Language. Cambridge: Cambridge Univrsity Press.

Nation, P., & Chung, T. (2009).Teaching and learning vocabulary. In Long, M, H., &

Nyikos, M. & Fan, M. (20007). Areview of Research on Vocabulary Learning Strategies. In A. Cohen and Macaro (Eds.), Language Learner Strategies.

O'mally, J.M. & Chamot A.U. (1990). Learning Strategies in Second Language Acquisition. Cambridge: Cambridge University Press. older students with reading difficulties.

Oxford, R. (1990). Language Learning Strategies: What Every Teacher Should Know. New York: Newbury House Publishers.

Oxford, R. (2003). Toward A more Systematic Model Pf L2 Learner Autonomy. In Palfreyman, P. and Smith, R. (Eds.). Learner Autonomy Across Culture: Language Education P erspectives, Great Britain: Pagrave Macmillan. pedagogy. Cambridge; University Press.

Oxford, R., & Schramm, K. (2007). Bridging the gap between Psychological and Sociocultural Perspectives on L2 Learner Strategies. In Cohen, A. D., & Macaro, E. (Eds.). (2007). Language earner Strategies: Thirty years of research and practice. Oxford, UK: Oxford University Press.

Pikulski,J, & Tempieton ,S.(2004).Teachig and Developing Vecabulary :Key to Long Term Reading Success."http://WWW.edupace.com/stat/author /piktemp/ pdf Practice.

Pratt.D,(1994).*Carriculum Planning A Hand Book Professionals*. New york ; Hareor brace College Puplishers Reading Education Reading Research Quarterly Research bases. In D. C. Simmons & E. J. Kame'enui (Eds.), What reading research.

Qian, D. (2002). Investigating The Relation ship Between Vocabulary Knoweledge and Academic P erformance: An Assessment Perspective. Language Learning,

Read, J. (2000). *Assessiing Vocabulary*. Cambridge: Cambridge UniversityPress.

Ricard ,J. (1985).*The Contex of Language Teaching.* Cambridge Cup.

Richards ,J. C. & T. Rodgers (2001).*Approaches and Methods in Language. Teaching* (6th ed) Delhi :Cambrige University Press,

Richards ,J. & Renandya ,W .(2002). *Methodology in Language eaching: Antology of Currnt Practice.* Cambridge University Press.

Richards, J.C.,& Renandya,W.A. (2002). *Methodology in language teaching*.

Richards. & Rodgers,T(1986) Approaches and Methods in Language Teaching, Cambridge, and Cambridge፣ University press.

Rubin, J.(1987). Learner Strategies: Theoretical Assumption, Research History and Typology. In A. wenden and J. Rubin (eds.). *Learner Strategies in Language Learning.* (pp.107-160). Cambridge: Cambridge University Press.

Rupley, W. H., & Nichols, W. D. (2005). Vocabulary instruction for the struggling reader.

Schmitt, N. (2000). *Vocabulary in Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Schmitt, N. (2014). Size and depth of vocabulary knowledge: What the research shows.

Scholfield, P.J. (1997). Vocabulary Reference Works in Foreign Language Learning. In Schmitt, N. and McCarthy, M. (Eds.), Vocabulary: Description, Acquisition and Pedagogy (pp. 279-302). Cambridge: Cambridge University Press. Schmitt, N. (1997).Vocabulary Learning Strategies. In N.Schmitt and M.McCarthy (Eds.). Vocabulary:

Discription, Acquisition and Pedagogy Cambridge: Cambridge University Press.

Seal, B. (1991). “vocabulary learning and teaching:” Incelce Murcia, M. (eds.) teaching English as second or foreign language. Boston: Heinle and Heinle publishers. Simmons, D., Hairrell, A., Edmonds, M., Vaughn, S., Larsen, R., Willson, V.

Sokmen, A. J. (1997).Current Trends in Teaching Second Languag Vocabulary. In N.Schmitt and M. Spanish Students. International Review of Social Sciences and Humanities. Strategies of Arab EFL Readers. (Unpublished Ph.D. Dessertaion). University of Essex, Colchester.

Tonjes, M.J. (1991). *Secondary Reading, Writing, and Learning*. Boston: Allyn and Bacon.

Tudor, Ian.(1996). Learner-Centeredness as Language Education. Cambridge: Cambridge University Press. Ur ,P.(1996).A Courecin Languasge Teaching : Practice and Theory .Cambrige:Cup.

Vygotsky, L.S. (1978). Mind in Society: The Development of Higher Psychological processes. Cambridge, MA: Harvard University Press.

